https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ነሀሴ ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23[rd] Year, No.82
ADDIS ABABA,24[th], August , 2017

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲/፪ሺ፱ ዓ.ም

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ…………………………………………...ገጽ ፱ሺ፰፻፵፯
ሰንጠረዥ……………………………………ገጽ ፱ሺ፰፻፹፭

## CONTENT

Council of Ministers Regulation No.410 /2017

Council of Ministers Federal Income Tax Regulation………………………………………page 9847
Schedule……………………………………………………page 9885

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲/፪ሺ፱

### ስለፌዴራል የገቢ ግብር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ አንቀጽ ፺፱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር ፬፻፲/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.410/2017

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION ON THE FEDERAL INCOME TAX

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.916/2015 and Article 99 of the Federal Income Tax Proclamation No.979/2016.

### SECTION ONE

### GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Federal Income Tax Regulation No.410/2017".

**2. Definition**

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

https://chilot.me



፩/ "አዋጅ" ማለት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺ፰ ነው፤

፪/ "የተሻረው አዋጅ" ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ (እንደተሻሻለው)፣ የማዕድን ስራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለው) እና የነዳጅ ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፮/፲፱፻፸፰ (እንደተሻሻለው) ነው፤

፫/ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጐች እንደአግባብነቱ በአዋጁ ወይም በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺ፰ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በአዋጁ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሀረጎች አጠቃቀም

### ፫. ወለድ

ለአዋጁ ዓላማ በማንኛውም ስያሜ ቢጠቀስም በቁጠባና ብድር ማህበራት ለተቀማጭ ገንዘብ ወይም ለአባላት መዋጮ የሚፈጸም ክፍያ እንደወለድ ይቆጠራል፡፡

### ፬. በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፬(፪)(ሐ) ዓላማ ማንኛውም ሰው ከ ፩፻፹፫ ቀን በላይ መቆየቱን ለመወሰን የዚህ ሰው ወይም ግንኙነት ያለው ሰው ተያያዥ ፕሮጀክት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፬(፫) የተመለከተን ማንኛውም ግንባታ፣ፕሮጀክት ወይም ተያያዥ ሥራ የሚያከናውን ሰው ከ ፩፻፹፫ ቀን የሚበልጥ የቆይታ ጊዜ ማሟላቱን ለመወሰን፣ግንኙነት ባለው ሰው የተከናወነ ማንኛውም ግንባታ፣ፕሮጀክት ወይም ተያያዥ ሥራ መጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ያከናወነው ሥራ በወሰደው ጊዜ ላይ ተጨምሮ መሰላት አለበት፡፡

1/ "Proclamation" means the Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016;

2/ "Repealed Proclamation" means the Income Tax Proclamation No.286/2002 (as amended), the Mining Income Tax Proclamation No.53/1993 (as amended) and the Petroleum Operations Income Tax Proclamation No. 296/1986 (as amended);

3/ terms and phrases used shall have the same meaning as in the Proclamation or the Federal Tax Administration Proclamation No.983/2016, as the case may be.

## SECTION TWO

## APPLICATION OF TERMS USED IN THE PROCLAMATION

### 3. Interest

An amount, however described, paid by a saving and credit association as the return on deposits with, or member's contributions to the association shall be treated as interest for the purposes of this Proclamation.

### 4. Permanent Establishment

1/ In determining whether a person exceeds the 183-day period specified in Article 4(2)(c) of the Proclamation, account shall be taken of a connected project of the person or of a related person.

2/ When a person operates a building site or conducts a project or activity referred to in Article 4(3) of the Proclamation, any connected activities conducted by a related person shall be added to the period of time during which the first-mentioned person has operated the building site or conducted the project or activities for the purpose of determining whether the 183-day period is exceeded.

https://chilot.me



፭.ግለሰብ ነዋሪ

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ለአዋጁ አንቀጽ ፭(፪)(ሐ) ዓላማ አንድ ግለሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ለቆየባቸው ቀናት ስሌት፡-

ሀ) ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን እና ከኢትዮጵያ የወጣበትን ቀን ጨምሮ ማንኛውም ግለሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ የቆየበት ቀን ከፊል እንደሙሉ ቀን ቆይታ ይቆጠራል፤

ለ) ማንኛውም ግለሰብ በሙሉ ወይም በከፊል በኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘባቸው የሚከተሉት ቀናት እንደሙሉ ቀን ቆይታ ይቆጠራሉ፡-

(፩) የሕዝብ በዓላት፤
(፪) የእረፍት ቀናት፣የህመም ፈቃድን ጨምሮ፤
(፫) ግለሰቡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያከናውነው ሥራ በሥራ ማቆም አድማ፣በቀጣሪ በሚደረግ የሥራ መዝጋት፣ በግብዓት አቅርቦት መዘግየት፣ ሥራን በሚከለክል የአየር ሁኔታ ወይም ሥራን በሚያስተጓጉሉ ሌሎች ወቅታዊ ምክንያቶች የተቋረጠባቸው ቀናት፤
(፬) ግለሰቡ ማንኛውንም ሥራ ከመጀመሩ በፊት፣ በሥራ ላይ እያለ ወይም ሥራውን ከጨረሰ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፋቸው የእረፍት ቀናት፡፡

፪/ አንድ ግለሰብ ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች መካከል በሚያደርገው ጉዞ ምክንያት በተላላፊ መንገደኛነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርገው የሙሉ ወይም የከፊል ቀን ቆይታ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተደረገ ቆይታ አይቆጠርም፡፡

5. **Resident Individual**

1/ Subject to sub-article (2) of this Article, in calculating the number of days an individual is present in Ethiopia for the purposes of Article 5(2)(c) of the Proclamation:

a) a part of a day that an individual is present in Ethiopia (including the day of arrival in, and the day of departure from, Ethiopia) shall count as a whole day of such presence;

b) the following days in which an individual is wholly or partly present in Ethiopia shall count as a whole day of such presence:

(1) a public holiday;
(2) a day of leave, including sick leave;
(3) a day in which the individual's activity in Ethiopia is interrupted because of a strike, lock-out, delay in the receipt of supplies, adverse weather conditions, or seasonal factors;
(4) days spent by the individual on holiday in Ethiopia before, during, or after any activity conducted by the individual in Ethiopia.

2/ A day or part of a day when an individual is in Ethiopia solely by reason of being in transit between two different places outside Ethiopia shall not count as a day present in Ethiopia.

https://chilot.me



## ፮. አክሲዮኖች እና ቦንዶች

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፱(፯)(ሐ)“አክሲዮኖችን እና ቦንዶችን” በሚመለከት የተጠቀሰው ማንኛውንም በአክሲዮኖች ወይም ቦንዶች ላይ ያለን ባለአክሲዮን የመሆን መብትን ወይም ምርጫን የመሰለ ጥቅም ይጨምራል፡፡

፪/ በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነ ኩባንያ ውስጥ ያለን የአክሲዮን መብት ወይም በእንዲህ ዓይነቱ ኩባንያ የወጣን ቦንድ በማስተላፍ የተገኘ ጥቅም ከኢትዮጵያ ምንጭ እንደተገኘ ገቢ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የሠንጠረዥ “ሀ” ገቢ
## ንዑስ ክፍል አንድ
## የዓይነት ጥቅሞች

## ፯. የክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ ትርጓሜ

፩/ በዚህ ክፍል ውስጥ፡-

ሀ) “የሠራተኛ አክሲዮን ዕቅድ“ ማለት ቀጣሪ ኩባንያ ወይም ግንኙነት ያለው ኩባንያ ለቀጣሪ ኩባንያው ሠራተኛ አክሲዮን የሚደለድልበት ስምምነት ወይም አሠራር ነው፤

ለ) “የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ“ ማለት የቤት ሠራተኛ፣ምግብ አብሳይ ፣ሾፌር፣ አትክልተኛ፣ ወይም ሌላ ለቤተሰብ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤

ሐ) ከወር ጋር በተገናኘ “የገበያ የማበደሪያ ወለድ መጣኔ“ ማለት፡-

(፩) ለንግድ ባንክ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለንግድ ባንኮች ብድር እና በተላላፊ ሰነድ ዋስትና የሚሰጥ የቅናሽ ወለድ ብድር አቅርቦት በሰጠበት ወር በኢትዮጵያ ውስጥ የዋለው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ፣ ወይም

## 6. Shares and Bonds

1/ The reference to “shares and bonds” in Article 59(7)(c) of the Proclamation includes any interest in shares or bonds, such as, in the case of shares, a right or option to acquire shares.

2/ A gain arising on disposal of an interest in a share in, or a bond issued by, a resident company shall be Ethiopian source income.

## SECTION THREE
## SCHEDULE ‘A’ INCOME
## SUB-SECTION ONE
## FRINGE BENEFITS

## 7. Sub-Section One of Section Three Definition

1/ In this Section:

a) “employee share scheme” means an agreement or arrangement under which an employer company or a related company may allot shares to an employee of the employer company;

b) “household personnel” means a housekeeper, cook, driver, gardener, or other domestic assistant;

c) “market lending rate”, in relation to a month, means:

(1) for a commercial bank, the lending rate on loans and rediscount facilities granted by the National Bank of Ethiopia to commercial banks that prevailed in Ethiopia during the month; or

https://chilot.me



(፪) ለሌላ ማንኛውም ሰው ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በወሩ የዋለው ዝቅተኛው የንግድ ባንኮች የማበደሪያ ወለድ መጣኔ፣

ነው፤

መ) “ግንኙነት ያለው ኩባንያ“ ማለት ከኩባንያ ጋር በተገናኘ፣ ከመጀመሪያው ኩባንያ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው የሆነ ሌላ ኩባንያ ነው፤

ሠ) “ሩቅ ሥፍራ“ ማለት ሃያ ሺህ ነዋሪ ካለው የከተማ መሃል ሰላሳ ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኝ ሥፍራ ነው፤

ረ) “አገልግሎቶች“ ማለት በንብረት መጠቀምን እና ማንኛውንም መገልገያ ማቅረብን ይጨምራል፤

ሰ) “ተሽከርካሪ“ ማለት ከአንድ ቶን በታች እና ከዘጠኝ ያነሱ ተሳፋሪዎችን መጫን እንዲችል ሆኖ የተሰራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፡፡

፪/ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ፡-

ሀ) “ቀጣሪ” ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው እና ከቀጣሪው ወይም ከቀጣሪው ጋር ግንኙነት ካለው ሰው ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት እንደቀጣሪ የሚሠራን ሶስተኛ ወገን ይጨምራል፤

ለ) “ተቀጣሪ” ከተቀጣሪው ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው ይጨምራል፡፡

**፰.** **<u>የዓይነት ጥቅሞች</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአዋጁ አንቀጽ ፲፪(፩)(ለ) ዓላማ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚሰጣቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጥቅሞች የዓይነት ጥቅሞች ናቸው:-

ሀ) ከዕዳ ነጻ የመደረግ፤

ለ) የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች፤

ሐ) የመኖሪያ ቤት፤

መ) የቅናሽ ወለድ ብድር፤

ሠ) የምግብ ወይም መጠጥ አገልግሎት፤

(2) for any other person, the lowest lending interest rate of commercial banks that prevailed in Ethiopia during the month;

d) “related company”, in relation to a company, means another company that is a related person in respect of the first-mentioned company;

e) “remote area” means a location that is thirty kilometres from an urban centre with a population of twenty thousand;

f) “services” include the use of property and the making available of any facility;

g) “vehicle” means a motor vehicle designed to carry a load of less than one tonne and fewer than nine passengers.

2/ In this Sub-section:

a) a reference to an “employer” includes a related person of the employer and a third party acting under an arrangement with an employer or a related person of the employer;

b) a reference to an “employee” includes a related person of the employee.

**8. <u>Fringe Benefits</u>**

1/ For the purposes of Article 12(1)(b) of the Proclamation and subject to this Article, benefits listed below which an employer provides to an employee are fringe benefits:

a) debt waiver;

b) household personnel;

c) housing;

d) discounted interest loan;

e) meal or refreshment;

https://chilot.me



ረ) የግል ወጪዎች፤

ሰ) የንብረት ወይም አገልግሎቶች፤

ሸ) የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ፤

ቀ) የተሽከርካሪ፤

በ) ሌላ የዓይነት ጥቅም፡፡

፪/ አንድ ተቀጣሪ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ፣ይህን ጥቅም ለማግኘት ያወጣው ወጪ የቅጥር ገቢን ለማግኘት ያደርገው የነበረ ወጪ እስከሆነ ድረስ እንደ ዓይነት ጥቅም አይቆጠርም፡፡

፫/ ማንኛውም ጥቅም የዓይነት ጥቅም መሆኑን እና የዓይነት ጥቅምን ዋጋ ለመወሰን ጥቅሙን በማስተላለፍ ረገድ የተጣለ ገደብ መኖሩ እና ጥቅሙ በሌላ ሁኔታ ወደገንዘብ መለወጥ አለመቻሉ ከግምት ውስጥ አይገባም፡፡

፬/ ለአዋጁ ወይም ለዚህ ደንብ ዓላማ የሚከተሉት ጥቅሞች እንደ ዓይነት ጥቅሞች አይቆጠሩም:-

ሀ) በአዋጁ ሠንጠረዥ “ሠ” መሠረት ከግብር ነጻ የተደረገ ጥቅም፤

ለ) ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ቀጣሪ ተመሳሳይ ጥቅም የሚያቀርብበትን ድግግሞሽ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዋጋው አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ማስላቱ ምክንያታዊ ያልሆነ እና ለአስተዳደር የማያመች ጥቅም፤

ሐ) በቀጣሪው ወይም በቀጣሪው ስም በሚተዳደር የሠራተኞች ምግብ ቤት፣ካፌቴሪያ ወይም የመመገቢያ ክፍል ያለምንም ልዩነት ለመደበኛ ሠራተኞች ጥቅም ብቻ ተብሎ የሚቀርብ የምግብና መጠጥ አገልግሎት ድጎማ፤

መ) በሚከተሉት ምንያቶች የሥራ አመራር አካል ላልሆነ ተቀጣሪ በሩቅ ሥፍራ የሚቀርብ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግሎት:-

f) private expenditure;

g) property or service;

h) an employee share scheme;

i) vehicle;

j) residual fringe benefit.

2/ A benefit is not a fringe benefit to the extent that, if the employee had acquired the benefit, the expenditure incurred by the employee in acquiring the benefit would have been incurred in deriving employment income.

3/ In determining whether a benefit is a fringe benefit and the value of a fringe benefit, any restriction on transfer of the benefit and the fact that the benefit is not otherwise convertible to cash are to be disregarded.

4/ The following benefits are not treated as fringe benefits for the purposes of the Proclamation or this Regulation:

a) a benefit that is exempted income under Schedule ‘E’ of the Proclamation;

b) a benefit the value of which, after taking into account the frequency with which the employer provides similar benefits, is so small as to make accounting for it unreasonable or administratively impracticable in accordance with the directive to be issued by the Minister;

c) subsidy to a meal or refreshment provided in a canteen, cafeteria, or dining room operated by, or on behalf of, an employer solely for the benefit of employees and that is available to all non-casual employees on equal terms;

d) the provision of accommodation or housing to a non-managerial employee in a remote area if:

https://chilot.me



(፩) የተቀጣሪው መደበኛ የሥራ ቦታ በሩቅ ሥፍራ ስሆን፣ እና

(፪) በቀጣሪው የሥራ ባህሪ ምክንያት ሠራተኛው በየጊዜው ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ወይም በሩቅ ሥፍራው በቂ የሆነ ምቹ ማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤት ባለመኖሩ ቀጣሪው ማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤት ማቅረቡ አስፈላጊ ስለሆነ፣

ሠ) ተቀጣሪው እንዲጠቀምበት በቀጣሪው የሚቀርብ ተንቀሳቃሽ ስልክ፤

ረ) በቀጣሪው በቀረበ የተንቀሳቃሽ ስልክ የተደረገን ጥሪ ጨምሮ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚሸፍነው የተንቀሳቃሽ ስልክ ጥሪዎች ወጪ፤

ሰ) በዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ ወይም የጎልማሶች ትምህርት በሚሰጥ ሌላ ተቋም የሚሰጥ ትምህርት መከታተል እንዲችል ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚፈጽመው የትምህርት ወይም ሥልጠና ክፍያ፤

ሸ) ለተቀጣሪ ጥቅም የሚቀርብ የደህንነት ጥበቃ አገልግሎት፤

ቀ) ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ተቋሞች ለተቀጣሪዎቻቸው የሚያቀርቡት የምግብና መጠጥ አገልግሎት፤

በ) ለተቀጣሪዎች የሚቀርብ የደንብ ልብስ እና የሥራ መገልገያ::

**፱. <u>ከዕዳ ነጻ የመደረግ የዓይነት ጥቅም</u>**

፩/ ተቀጣሪ ለቀጣሪ መክፈል ያለበትን ዕዳ ወይም መመለስ የሚኖርበትን የብድር ግዴታ ቀጣሪ ቀሪ ማድረጉ ከዕዳ ነጻ የመደረግ የዓይነት ጥቅም ነው።

(1) the employee's usual place of employment is in the remote area; and

(2) it is necessary for the employer to provide the accommodation or housing to the employee in the remote area because the nature of the employer's business is such that the employee is likely to move frequently from one residential location to another or there is insufficient suitable residential accommodation available in the remote area;

e) the provision of a mobile phone by an employer for use by an employee;

f) the payment by an employer of the cost of mobile phone calls made by an employee, including with a mobile phone provided by the employer;

g) tuition fees paid by an employer for the benefit of an employee for attendance at a course offered by a university, college, or other institution providing adult education courses;

h) the provision of the services of a security guard for the benefit of an employee;

i) the provision of food and beverage services by Hotels, Restaurants and other similar establishments for their employees;

j) the provision of uniforms and related work materials.

**9. <u>Debt Waiver Fringe Benefit</u>**

1/ The waiver by an employer of the obligation of an employee to pay or repay an amount owing to the employer is a debt waiver fringe benefit.

https://chilot.me



፪/ ከዕዳ ነጻ የመደረግ የዓይነት ጥቅም ዋጋ ቀሪ የተደረገው የዕዳ መጠን ነው፡፡

**፲. <u>የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች የዓይነት ጥቅም</u>**

የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች የዓይነት ጥቅም ዋጋ ተቀጣሪው ላገኘው የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች አገልግሎት ቀጣሪው በወሩ በከፈለው ጠቅላላ የቅጥር ገቢ እና ተቀጣሪው ለእነዚሁ አገልግሎቶች በከፈለው መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

**፲፩. <u>የመኖሪያ ቤት ወይም የማረፊያ የዓይነት ጥቅም</u>**

፩/ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበው የመኖሪያ ቤት የዓይነት ጥቅም ዋጋ፣ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤቱ ባለቤት ቀጣሪ ሲሆን በወሩ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤቱ ትክክለኛ የገበያ ኪራይ እና ተቀጣሪው ለማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤቱ በከፈለው መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

፪/ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበው የመኖሪያ ቤት የዓይነት ጥቅም ዋጋ፣ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤቱን ቀጣሪው የተከራየው ሲሆን ቀጣሪው በወሩ ለማረፊያ ወይም ለመኖሪያ ቤቱ በከፈለው ኪራይ እና ተቀጣሪው ለማረፊያ ወይም መኖሪያ ቤቱ በከፈለው የኪራይ መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

**፲፪. <u>የቅናሽ ወለድ ብድር የዓይነት ጥቅም</u>**

፩/ ቀጣሪ ለተቀጣሪ በሚሰጠው ብድር ላይ ተቀጣሪው የሚከፈለው ወለድ ከገበያው የማበደሪያ ወለድ መጣኔ የሚያንስ ከሆነ የቅናሽ ወለድ ብድር የዓይነት ጥቅም ነው፡፡

፪/ የቅናሽ ወለድ ብድር የዓይነት ጥቅም ዋጋ ተቀጣሪው በወሩ በብድሩ ላይ ወለድ የከፈለ ከሆነ፣ በወሩ በከፈለው ወለድ እና ብድሩን የወሰደው በገበያ የማበደሪያ ወለድ መጣኔ ቢሆን ኖሮ በወሩ ይከፍል በነበረው ወለድ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

**፲፫. <u>የምግብ ወይም የመጠጥ አገልግሎት የዓይነት ጥቅም</u>**

ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበው የምግብ ወይም መጠጥ

2/ The value of a debt waiver fringe benefit shall be the amount waived.

**10. <u>Household Personnel Fringe Benefit</u>**

The value of a household personnel fringe benefit for a month shall be the total employment income paid to the household personnel in that month for services rendered to the employee reduced by any payment made by the employee for such services.

**11. <u>Housing or Accommodation Fringe Benefit</u>**

1/ The value of a housing fringe benefit provided by an employer to an employee for a month when the employer owns the accommodation or housing shall be the fair market rent of the accommodation or housing for the month reduced by any payment made by the employee for the accommodation or housing.

2/ The value of a housing fringe benefit provided by an employer to an employee for a month when the employer leases the accommodation or housing shall be the rent paid by the employer for the accommodation or housing during the month reduced by any payment made by the employee for the accommodation or housing.

**12. <u>Discounted Interest Loan Fringe Benefit</u>**

1/ A loan provided by an employer to an employee is a discounted interest loan fringe benefit if the interest rate under the loan is less than the market lending rate.

2/ The value of a discounted interest loan fringe benefit for a month shall be the difference between the interest paid by the employee on the loan for the month, if any, and the interest that would have been paid by the employee on the loan for the month if the loan had been made at the market lending rate for that month.

**13. <u>Meal or Refreshment Fringe Benefit</u>**

The value of a meal or refreshment fringe benefit shall

https://chilot.me



አገልግሎት የዓይነት ጥቅም ዋጋ ቀጣሪው የምግብ ወይም የመጠጥ አገልግሎቱን ለማቅረብ ባወጣው ጠቅላላ ወጪ እና ተቀጣሪው ለምግብ ወይም ለመጠጥ አገልግሎቱ በከፈለው የገንዘብ መጠን መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

**፲፬.የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም**

፩/ ቀጣሪ በሙሉ ወይም በከፊል ለተቀጣሪ የግል ጥቅም የሚያቀርበው ተሽከርካሪ የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣የወር የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም ዋጋ በሚከተለው ቀመር መሠረት የተሰላው የገንዘብ መጠን ይሆናል:-

$$\frac{ሀ \times 5\%}{12}$$

ለዚህም፡- "ሀ" ቀጣሪ የተሽከርካሪው ባለቤት ለመሆን ያወጣው ወጪ ወይም ቀጣሪው ተሽከርካሪውን ተከራይቶ ከሆነ፣ ተሽከርካሪውን በተከራየበት ጊዜ የነበረው የተሽከርካሪው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው፤ ሆኖም ተሽከርካሪው ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆኖ የገባ እንደሆነ የተሽከርካሪው የዓይነት ጥቅም ዋጋ ተሽከርካሪው ከቀረጥና ታክስ ነጻ ባይደረግ ኖሮ በተሽከርካሪው ላይ ይከፈል የነበረውን ቀረጥና ታክስ መጠን ይጨምራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከሚሰላው የተሽከርካሪ የዓይነት ጥቅም ዋጋ ላይ የሚከተሉት ተቀናሽ ይደረጋሉ:-

ሀ) በተሽከርካሪው ለመጠቀም ወይም ለተሽከርካሪው ጥገና እና የመጠቀሚያ ወጪ ተቀጣሪው የፈፀመው ማንኛውም ክፍያ፤

ለ) ተቀጣሪው ሥራውን ለማከናወን ተሽከርካሪውን የተጠቀመበት መጠን፤

ሐ) በወር ውስጥ ተሽከርካሪው ለተቀጣሪው የግል ጥቅም ያልቀረበበት መጠን፡፡

be the total cost to the employer of providing the meal or refreshment reduced by any amount paid by the employee for the meal or refreshment.

**14. Vehicle Fringe Benefit**

1/ A vehicle provided by an employer to an employee wholly or partly for the private use of the employee is a vehicle fringe benefit.

2/ Subject to sub-articles (3) and (4) of this Article, the value of a vehicle fringe benefit for a month shall be the amount calculated in accordance with the following formula:

$$\frac{(A \times 5\%)}{12}$$

Where: "**A**" is the cost to the employer of acquiring the vehicle or, if the vehicle is leased by the employer, the fair market value of the vehicle at the commencement of the lease. However, in case of a vehicle imported free of duty and taxes, the value of the vehicles' fringe benefit shall include the duty and taxes that would otherwise have been paid on the vehicle.

3/ From the value of a vehicle fringe benefit calculated under sub-article (2) of this Article the following shall be reduced:

a) any payment made by the employee for the use of the vehicle or for maintenance and running costs;

b) the proportion of the use of the vehicle (if any) by the employee in the conduct of employment;

c) the proportion of the month (if any) that the vehicle was not provided to the employee for private use.

https://chilot.me



፬/ ተሽከርካሪው በቀጣሪው ይዞታ ስር ከአምስት ዓመት በላይ የቆየ ከሆነ፣ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፪) ቀመር ሥር የተመለከተው የ"ሀ" ዋጋ በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚወሰነው የገንዘብ መጠን ፶ በመቶ (ሃምሳ በመቶ) ይሆናል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ "ለተቀጣሪ የግል ጥቅም የቀረበ ተሽከርካሪ" የሚለው አገላለጽ ተቀጣሪው ተሽከርካሪውን በማንኛውም ጊዜ ለግል ጉዳይ ባይጠቀምበትም ለተቀጣሪ የግል ጥቅም የቀረበን ተሽከርካሪ ይጨምራል፡፡

**፲፭.<u>የግል ወጪዎች የዓይነት ጥቅም</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ለተቀጣሪው የግል ጥቅም የሚያስገኝ እስከሆነ ድረስ በቀጣሪ ለግል ወጪ የተከፈለ ገንዘብ የግል ወጪ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡

፪/የግል ወጪ የዓይነት ጥቅም ዋጋ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት እንደ ግል ወጪ የዓይነት ጥቅም የሚቆጠር ወጪ መጠን ይሆናል፡፡

፫/ ይህ አንቀጽ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚከፍለውን በዚህ ደንብ ከአንቀጽ ፲፰ ከተመለከተው በስተቀር በዚህ ክፍል በሌላ አንቀጽ የዓይነት ጥቅም ነው የተባለን ወጪ አይመለከትም፡፡

**፲፮.<u>የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም</u>**

፩/ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያስተላልፈው ንብረት ወይም የሚያቀርበው አገልግሎት የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም ነው፡፡

፪/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም:-

ሀ) ቀጣሪ ንብረቱን ወይም አገልግሎቱን እንደመደበኛ ሥራው ለደንበኞች የሚያቀርብ ከሆነ የንብረቱን ወይም የአገልግሎቱ መሸጫ ዋጋ ፸፭ በመቶ ( ሰባ አምስት በመቶ)፣ ወይም

4/ If an employer has held a vehicle for more than five years, the value of component "**A**" in the formula under sub-article (2) of this Article shall be 50% of the amount determined under sub-article (2).

5/ A reference in this Article to "a vehicle being provided to an employee for private use" includes a vehicle that is made available to an employee for private use even if the employee did not actually use the vehicle for a private use at any time.

**15. <u>Private Expenditure Fringe Benefit</u>**

1/ Subject to sub-article (3) of this Article, the payment of expenditure by an employer is a private expenditure fringe benefit to the extent that the expenditure gives rise to a private benefit to an employee.

2/ The value of a private expenditure fringe benefit shall be the amount of the expenditure treated as a private expenditure fringe benefit under sub-article (1) of this Article.

3/ This Article shall not apply to expenditure paid by an employer that is a fringe benefit under another Article in this section other than Article 18 of this Regulation.

**16. <u>Property or Services Fringe Benefit</u>**

1/ The transfer of property or provision of services by an employer to an employee is a property or services fringe benefit.

2/ Subject to sub-article (3) of this Article, the value of a property or services fringe benefit shall be:

a) if the employer supplies the property or services to customers in the ordinary course of business, 75% of the normal selling price of the property or services; or

https://chilot.me



ለ) በሌላ ሁኔታ የንብረቱ ወይም የአልግሎቱ መሸጫ ዋጋ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚወሰነው የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም ዋጋ ተቀጣሪው ለንብረቱ ወይም ለአገልግሎቱ በከፈለው የገንዘብ መጠን ይቀነሳል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ሀ) ዓላማ የንብረት ወይም የአገልግሎት የዓይነት ጥቅም የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ ቀጣሪ የሚሰጠው ነጻ ወይም ድጎማ የተደረገበት የአየር ጉዞ ትኬት ከሆነ፣ የትኬቱ የመሸጫ ዋጋ ቀጣሪው ለበረራው የኢኮኖሚ ደረጃ የሚያስከፍለው መደበኛ ዋጋ ይሆናል፡፡

**፲፯.የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ የዓይነት ጥቅም**

፩/ ባለአክሲዮን የመሆን መብትን ወይም ምርጫን በመጠቀም የተደለደሉ አክሲዮኖችን ጨምሮ በሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ መሠረት ለተቀጣሪ አክሲዮን መደልደል የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡

፪/ በሠራተኛ የአክሲዮን ዕቅድ መሠረት ለተቀጣሪ የሚሰጥ ባለአክሲዮን የመሆን መብት ወይም ምርጫ ዋጋ እንደ ዓይነት ጥቅም አይቆጠርም ወይም ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ውስጥ አይካተትም፤ሆኖም፡-

ሀ) ተቀጣሪው በመብቱ ወይም በምርጫው የሚጠቀም ከሆነ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ይሆናል፤ ወይም

ለ) ተቀጣሪው መብቱን ወይም ምርጫውን የሚያስተላልፍ ከሆነ መብቱ ወይም ምርጫው በምድብ “ለ” ሥር ግብር እንደሚከፈልበት ሀብት ተቆጥሮ የአዋጁ አንቀጽ ፶፱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሠራተኞች የአክሲዮን ዕቅድ የዓይነት ጥቅም ዋጋ አክሲዮኖች በተደለደሉበት ቀን በነበራቸው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ እና ተቀጣሪው ለአክሲዮኖች በከፈለው መዋጮ መካከል ያለው

b) in any other case, the cost to the employer of acquiring the property or services.

3/ The value of a property fringe benefit determined under sub-article (2) of this Article shall be reduced by any payment made by the employee for the property or services.

4/ For the purposes of sub-article (2)(a) of this Article, if the property or services fringe benefit is the provision of free or subsidised air travel by an employer that is an airline operator, the normal selling price is the standard economy fare for the flight provided by the employer.

**17. Employees' Share Scheme Benefit**

1/ The allotment of shares to an employee under an employee share scheme, including shares allotted as a result of the exercise of an option or right to acquire the shares, is an employee share scheme fringe benefit.

2/ The value of a right or option to acquire shares granted to an employee under an employee share scheme shall not be treated as a fringe benefit or otherwise included in employment income:

a) if the employee exercises the right or option, this Article applies to; or

b) if the employee disposes of the right or option, Article 59 of the Proclamation shall apply to the disposal on the basis that the right or option is a class 'B' taxable asset.

3/ Subject sub-article (4) of this Article, the value of an employee share scheme fringe benefit shall be the fair market value of the shares at the date of allotment reduced by the employees' contribution for the shares.

https://chilot.me



ልዩነት ይሆናል፡፡

፬/ በሠራተኞች የአክሲዮን ዐቅድ መሠረት ለተቀጣሪ የተደለደሉ አክሲዮኖች ለሌላ ሰው የመተላለፍ ገደብ የተጣለባቸው ከሆነ፣ተቀጣሪው የአክሲዮን ዐቅድ ጥቅሙን ያገኘው:-

ሀ) አክሲዮኖቹን ያለገደብ ማስተላለፍ በሚችልበት፣ ወይም

ለ)አክሲዮኖቹን በሚያስተላልፍበት፣

ከሁለቱ በቀደመው ጊዜ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የአክሲዮኑ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ በዚሁ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት የሠራተኞች ዐቅድ ጥቅሙ በተገኘበት ጊዜ ይወሰናል፡፡

፮/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ በሠራተኞች የአክሲዮን ዐቅድ መሠረት ለተቀጣሪ ከተደለደሉ አክሲዮኖች ጋር በተገናኘ "የተቀጣሪ መዋጮ" ማለት ተቀጣሪው፣

ሀ) ለአክሲዮኖቹ፣ እና

ለ) ባለአክሲዮን ለመሆን ለተሰጠው መብት ወይም ምርጫ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

## ፲፰.ሌላ የዓይነት ጥቅም

፩/ "ሌላ የዓይነት ጥቅም" ማለት ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚያቀርበውና በዚህ ክፍል ሌሎች አንቀጾች ያልተመደበ የዓይነት ጥቅም ነው፡፡

፪/ የሌላ የዓይነት ጥቅም ዋጋ ጥቅሙ የተገኘበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ በሚወሰን የጥቅሙ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ እና ተቀጣሪ ለጥቅሙ በፈፀመው ማንኛውም ክፍያ መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡

## ፲፱. በዓይነት ጥቅም ላይ የተጣለ የግብር ገደብ

፩/ በዚህ ምዕራፍ የተደነገገው ቢኖርም በዓይነት ጥቅሞች ላይ የሚከፈለው ጠቅላላ ግብር በማንኛውም ሁኔታ ተቀጣሪው በወሩ ከሚያገኘው የደመወዝ ገቢ ፲ በመቶ (አስር በመቶ) መብለጥ የለበትም፡፡

4/ If shares allotted to an employee under an employee share scheme are subject to a restriction on the transfer of the shares, the employee is treated as having derived the employee share scheme benefit on the earlier of:

a) the time the employee is able to freely transfer the shares; or

b) the time the employee disposes of the shares.

5/ When sub-article (4) of this Article applies, the fair market value of the shares is determined at the time the employee share scheme benefit is derived as determined under this sub-article (4).

6/ In this Article, "employees' contribution", in relation to shares allotted to an employee under an employee share scheme, means the sum of the consideration, if any, given by the employee:

a) for the shares; and

b) for the grant of any right or option to acquire the shares.

## 18. Residual Fringe Benefit

1/ A benefit provided by an employer to an employee not covered by another Article in this section is a residual fringe benefit.

2/ The value of a residual fringe benefit is the fair market value of the benefit determined at the time it is provided, as reduced by any payment made by the employee for the benefit

## 19. Limitation of Tax Liability on Fringe Benefits

1/ Notwithstanding the provisions of this sub-section, the aggregate tax liability on fringe benefits shall under any circumstance not exceed 10% of the salary income of the employee.

https://chilot.me



፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ደመወዝ ከቅጥር ጋር የተያያዙ ሌሎች ጥቅማጥቅሞች አይጨምርም፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ከውጭ ሀገር የተገኘ የቅጥር ገቢ**

**፳. በውጭ ሀገር ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ**

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፺፫(፩) በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ቀጣሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ላቋቋመው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የተቀጠረን ሰው ሳይጨምር በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ባልሆነ ሰው በተቀጠረ የኢትዮጵያ ነዋሪ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ተቀጣሪ በማንኛውም ወር በውጭ ሀገር በመቀጠር ገቢ ያገኘ እና በዚሁ ገቢ ላይ በውጭ ሀገር ግብር የከፈለ እንደሆነ፣ ተቀጣሪው ከሚከተሉት ከሚያንሰው ጋር እኩል በሆነ መጠን የግብር ማካካሻ የማግኘት መብት ይኖረዋል:-

ሀ) ውጭ ሀገር የከፈለው ግብር፣ ወይም

ለ) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነው ተቀጣሪ የውጭ ሀገር ገቢ ላገኘበት ወር ተፈጻሚ በሚሆነው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔን መሠረት በማድረግ የሚሰላው ተቀጣሪው በውጭ ሀገር ገቢው ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፍለው ግብር፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ለተፈቀደው የግብር ማካካሻ አፈጻጸም "የንግድ ሥራ ገቢ ግብር" በሚል የተጠቀሰው "ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ግብር" እንዲሁም "የግብር ዓመት" በሚል የተጠቀሰው "ለወር" እንደሚያገለግል በመውሰድ የአዋጁ አንቀጽ ፵፭(፫)፣(፬) እና (፭) ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም:-

ሀ) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ተቀጣሪን በሚመለከት "ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔ" ማለት ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት ተቀጣሪው በወር ግብር በሚከፍልበት ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ሊከፍል

2/ For the purpose of this Article "salary" doesn't include other employment related benefits.

**SUB-SECTION TWO**

**FOREIGN EMPLOYMENT INCOME**

**20. Foreign Employment Income**

1/ Article 93(1) of the Proclamation shall apply to a resident employee employed by a non-resident employer otherwise than as an employee of an Ethiopian permanent establishment of the non-resident.

2/ If a resident employee has derived foreign employment income for a calendar month on which the employee has paid foreign income tax, the employee shall be allowed a tax credit of an amount equal to the lesser of:

a) the foreign income tax paid; or

b) the employment income tax payable in respect of the foreign employment income calculated by applying the average rate of employment income tax applicable to the resident employee to the foreign employment income of the employee for the month.

3/ Article 45(3), (4), and (5) of the Proclamation shall apply for the purposes of the tax credit allowed under this Article on the basis that the reference to "business income tax" is a reference to "employment income tax" and the reference to "tax year" is a reference to the "calendar month".

4/ In this Article:

a) "average rate of employment income tax", in relation to a resident employee for a calendar month, means the percentage that the employment income tax payable by the employee for the month, before the allowance

https://chilot.me



የሚገባው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር መቶኛ ነው፤

ለ) “በውጭ ሀገር ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ“ ማለት በአዋጁ ሠንጠረዥ “ሀ“ መሠረት ግብር የሚከፈልበት የውጭ ሀገር ገቢ ነው፤

ሐ) “የውጭ ሀገር ገቢ ግብር“ ማለት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር አካባቢያዊ መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ ቅጣትን፣ ተጨማሪ ግብርን ወይም ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም፡፡

መ) “ነዋሪ ተቀጣሪ“ ማለት በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ተቀጣሪ ነው፡፡

## ክፍል አራት
## የሠንጠረዥ “ለ” ገቢ

### ፳፩.ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የኪራይ ክፍያ

የአዋጁ አንቀጽ ፲፭(፭) ተፈጻሚ የሚሆንበት አከራይ ወይም የተከራይ አከራይ ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸርን የቤት ኪራይ ገቢ የተቀበለ እንደሆነ፣ አከራዩ ወይም የተከራይ አከራዩ በዚህ ዓይነት የተቀበለው ጠቅላላ የቤት ኪራይ ገቢ መጠን፣ ገቢውን በተቀበለበት የግብር ዓመት እንደተገኘ ተደርጎ ይቆጠራል፤ ሆኖም በዚህ የገቢ መጠን ላይ የሚከፈለው ግብር የቤት ኪራይ ገቢው ለሚሸፍነው የግብር ዓመታት በማከፋፈል ይሰላል፡፡

### ፳፪. የንግድ ሥራ ሀብቶች ኪራይ

የንግድ ሥራ መደበኛ ተግባር አካል የሆኑ ዕቃዎችን፣ መሣሪያዎችን እና ቤቶችን ጨምሮ የንግድ ሥራን በማከራየት የሚገኝ ገቢ በአዋጁ ሠንጠረዥ “ሐ“ መሠረት ግብር ይከፈልበታል፡፡

of any tax credit, is of the total employment income of the employee for the month;

b) “foreign employment income” means foreign income that is taxable under Schedule ‘A’ of the Proclamation;

c) “foreign income tax” means income tax, including withholding tax, imposed by the government of a foreign country or a political subdivision of a government of a foreign country, but does not include a penalty, additional tax, or interest payable in respect of such tax;

d) “resident employee” means an employee who is a resident of Ethiopia.

## SECTION FOUR
## SCHEDULE ‘B’ INCOME

### 21.Rental Payment Covering More Than One Year

If a lessor or sub-lessor to whom Article 15(5) of the Proclamation applies receives an amount of rental income for a period in excess of one year, the total amount of rental income received shall be treated as having been derived in the tax year in which it was received but the tax payable on the amount shall be calculated by prorating the rental income over the number of tax years to which the payment relates.

### 22. Lease of Business Assets

Income derived from the lease of a business, including goods, equipment, and buildings that are part of the normal operation of a business, shall be taxable under Schedule ‘C’ of the Proclamation.

https://chilot.me



**፳፫. <u>የኪራይ ቤት፣ የቤት ዕቃና መሣሪያ የእርጅና ቅናሽ</u>**

ለአዋጁ አንቀጽ ፲፭(፯)(ሐ) ዓላማ በአንድ የግብር ዓመት ለኪራይ ቤት፣ ለቤት ዕቃና መሣሪያ የተፈቀደው የእርጅና ቅናሽ የሚወሰነው በአዋጁ አንቀጽ ፳፭ እና በዚህ ደንብ ክፍል አምስት ንዑስ ክፍል ሁለት መሠረት ሆኖ፣ የሚከተሉትን መሠረት በማድረግ ይሆናል:-

፩/ የኪራይ ቤቱ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ሆኖ፣ ለማይንቀሳቀስ ንብረት መዋቅራዊ ማሻሻያ የተደረገ መሆኑን፤

፪/ ከቤቱ ጋር የተከራየ ማንኛውም የቤት ዕቃ እና መሣሪያ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት መሆኑን፡፡

**፳፬. <u>የቤት ኪራይ ኪሣራዎች</u>**

፩/ የሂሣብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት በአዋጁ አንቀጽ ፲፭(፯)(ሐ) መሠረት የተፈቀደለት ተቀናሽ ወጪ ከግብር ዓመቱ ጠቅላላ የቤት ኪራይ ገቢው የሚበልጥ ከሆነ፣ በብልጫ የሚታየው የገንዘብ መጠን በግብር ዓመቱ እንደደረሰ የቤት ኪራይ ኪሳራ ይቆጠራል፡፡

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፮ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፪ “ኪሣራ” በሚል የተጠቀሰው “ለቤት ኪራይ ኪሣራ” እንደሚያገለግል በመውሰድ እነዚህ አንቀጾች የቤት ኪራይ ኪሣራ ለደረሰበት ግብር ከፋይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፳፭.<u>ከውጭ ሀገር የቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ</u>**

፩/ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ግብር ከፋይ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ ያለው እና በዚሁ ገቢ ላይ በውጭ ሀገር ግብር የከፈለ እንደሆነ፣ግብር ከፋዩ ከሚከተሉት ከሚያንሰው ጋር እኩል በሆነ መጠን የግብር ማካካሻ የማግኘት መብት ይኖረዋል:-

ሀ) ውጭ ሀገር የከፈለው ግብር፤ ወይም

ለ)ግብር ከፋዩ የተጣራ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ ላገኘበት የግብር ዓመት ተፈጻሚ በሚሆነው

**23. <u>Depreciation of a Rental Building, Furniture, and Equipment</u>**

For the purposes of Article 15(7)(c) of the Proclamation, the deduction allowed for a tax year for depreciation of a rental building, furniture, and equipment shall be determined in accordance with Article 25 of the Proclamation and Sub-section Two of Section Five of this Regulation on the basis that:

1/ the rental building is a depreciable asset being a structural improvement to immovable property; and

2/ any furniture and equipment leased with the building are depreciable assets.

**24. <u>Rental Income Losses</u>**

1/ If the total rental income for a tax year of a taxpayer keeping records is exceeded by the deductions allowed to the taxpayer under Article 15(7)(c) of the Proclamation for the tax year, the amount of the excess shall be treated as a rental loss for the year.

2/ Article 26 of the Proclamation and Article 42 of this Regulation shall apply to a taxpayer who has a rental loss on the basis that the reference in those Articles to a “loss” is a reference to a “rental loss”.

**25. <u>Foreign Rental Income</u>**

1/ If a resident taxpayer has foreign rental income for a tax year on which the taxpayer has paid foreign income tax, the taxpayer shall be allowed a tax credit of an amount equal to the lesser of:

a) the foreign income tax paid; or

b) the rental income tax payable in respect of the foreign rental income of the taxpayer

https://chilot.me



ከቤት ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔን መሠረት በማድረግ የሚሰላው ግብር ከፋዩ በውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢው ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፍለው ግብር፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ለተፈቀደው የግብር ማካካሻ አፈጻጸም "የንግድ ሥራ ገቢ ግብር" በሚል የተጠቀሰው "ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ ግብር" እንደሚያገለግል በመውሰድ የአዋጁ አንቀጽ ፵፭(፫)፣(፬) እና (፭) ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም:-

ሀ) በአንድ የግብር ዓመት የኢትዮጵያ ነዋሪን በሚመለከት "ከቤት ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር የማስከፈያ አማካይ መጣኔ" ማለት ማንኛውም የግብር ማካካሻ ከመደረጉ በፊት በግብር ዓመቱ ነዋሪው ግብር በሚከፍልበት ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቤት ኪራይ ገቢ ግብር መቶኛ ነው፤

ለ) "የውጭ ሀገር ገቢ ግብር" ማለት በከፋዩ ተቀንሶ የሚያዝን ግብር ጨምሮ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር የክልል መንግሥት የተጣለ ግብር ሲሆን፣ ቅጣትን፣ ተጨማሪ ግብርን ወይም ይህንን ግብር በሚመለከት የሚከፈል ወለድን አይጨምርም፤

ሐ) "በውጭ ሀገር ከቤት ኪራይ የሚገኝ ገቢ" ማለት በአዋጁ ሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ግብር የሚከፈልበት የውጭ ሀገር ገቢ ነው፤

መ) በአንድ የግብር ዓመት የኢትዮጵያ ነዋሪ ግብር ከፋይን በሚመለከት "የተጣራ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ" ማለት ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ካገኘው ጠቅላላ የውጭ ሀገር የቤት ኪራይ ገቢ ላይ ገቢውን ከማግኘት ጋር በተገናኘ በአዋጁ አንቀጽ ፲፭(፯) መሠረት የተፈቀዱ ተቀናሽ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገቢ ነው፡፡

calculated by applying the average rate of rental income tax applicable to the taxpayer to the net foreign rental income of the taxpayer for the tax year.

2/ Article 45(3), (4), and (5) of the Proclamation shall apply for the purposes of the tax credit allowed under this Article on the basis that the reference to "business income tax" is a reference to "rental income tax".

3/ In this Article:

a) "average rate of rental income tax",in relation to a resident of Ethiopia for a tax year, means the percentage that the rental income tax payable by the resident for the year, before the allowance of any tax credit, is of the taxable rental income of the resident for the year;

b) "foreign income tax" means income tax, including withholding tax, imposed by the government of a foreign country or a political subdivision of a government of a foreign country, but does not include a penalty, additional tax, or interest payable in respect of such tax;

c) "foreign rental income" means foreign income taxable under Schedule 'B'; and

d) "net foreign rental income", in relation to a resident taxpayer for a tax year, means the total foreign rental income of the taxpayer for the year reduced by the deductions allowed under Article 15(7) of the Proclamation that relate to the derivation of that income.

https://chilot.me



**፳፮. የሚከራይ አዲስ ቤትን ስለማስታወቅ**

ለአዋጁ አንቀጽ ፲፯(፩) አፈፃፀም የአዲስ ቤት ግንባታ መጠናቀቁን ወይም ቤቱ መከራየቱን የማሳወቂያ ጊዜ ግንባታው በተጠናቀቀ ወይም ቤቱ በተከራየ ከሁለቱ በቀደመው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የሠንጠረዥ “ሐ” ገቢ**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**ተቀናሽ ወጪዎች**

**፳፯.የውክልና ወጪ**

ለአዋጁ አንቀጽ ፳፯(፩)(ቀ) ዓላማ “የውክልና ወጪ” ማለት የግብር ከፋዩ ሠራተኛ የንግድ ሥራውን ለማስተዋወቅ እና ለማሳደግ እንግዶችን ከንግድ ሥራ ቦታው ውጪ ለመቀበል የሚያወጣው የመስተንግዶ ወጪ ነው፡፡

**፳፰.ለውጭ ሀገር አበዳሪ የተከፈለ ወለድ ተቀናሽ የሚደረግበት ሁኔታ**

በአዋጁ አንቀጽ ፳፫(፪)(ሀ)(፪) መሠረት ለውጭ ሀገር አበዳሪ የተከፈለ ወለድ ተቀናሽ ሊደረግ የሚችለው አበዳሪው ብድር ለመስጠት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኘበትን ሰነድ ቅጂ ተበዳሪው ለባለሥልጣኑ ካቀረበ ብቻ ነው፡፡

**፳፱.ለሠራተኞች የተደረገ የህክምና ወጪ**

በሠራተኞች የጤና ዐቅድ መሠረት ቀጣሪ በተቀጣሪ ስም የሚከፍለውን የጤና መድን አረቦን ጨምሮ ለሠራተኛው የህክምና አገልግሎት የሚያወጣው ወጪ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪(፩)(ሀ) መሠረት ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

**፴. የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ተቋሞች ለሠራተኞች የሚያቀርቡት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት**

፩/ ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች ወይም የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ተቋሞች ለሠራተኞቻቸው የሚያቀርቡት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ወጪ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪(፩)(ሀ) መሰረት ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

**26. Notification of Rental of New Building**

For the purpose of Article 17(1) of the Proclamation, the period of notification of the completion or rental of new building shall be within one month of the earlier of the completion or rental of such building.

**SECTION FIVE**

**SCHEDULE ‘C’ INCOME**

**SUB-SECTION ONE**

**DEDUCTIONS**

**27. Representation Expenditures**

For the purposes of Article 27(1)(i) of the Proclamation, “representation expenditures” shall mean hospitality expenditures incurred by an employee in receiving guests from outside the business for the purposes of promoting and enhancing the business.

**28. Deductibility of Interest Paid to a Foreign Lender**

Interest paid to a foreign lender referred to in Article 23(2)(a)(2) of the Proclamation shall be deductible only if the borrower has provided the Authority with a copy of the letter of authorization to provide loan issued by the National Bank of Ethiopia to the foreigner lender.

**29. Medical Expense Incurred for Employees’**

Medical expense incurred by an employer for his employee including premium payments made under employees’ health insurance scheme shall be deducted in accordance with Article 22(1)(a) of the Proclamation.

**30.Food and Beverage Services Provided by Establishments Engaged in the Provision of Food and Beverage Services**

1/ Expenditure incurred in the provision of food and beverage services by Hotels, Restaurants or other similar establishments for their employees shall be deducted in accordance with Article 22(1)(a) of the Proclamation.

https://chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀናሽ የሚደረገው ወጪ ገደብ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፴፩.የንግድ ሥራ ማስታወቂያ ወጪ**

በአዋጅ አንቀጽ ፳፪(፩) "ሀ" መሠረት የሚፈቀድ በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር የተደረገ የንግድ ሥራ ማስታወቂያ ወጪ የተቀናሽ ገደብ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፴፪. የተከራየውን የንግድ ሥራ ሀብት በራሱ ወጪ የሚያድስ፣ የሚጠግን ወይም የሚያሻሽል ተከራይ**

ከአከራዩ ጋር ከገባው ውል ውጪ በገዛ ፈቃዱ የተከራየውን የንግድ ሥራ ሀብት በራሱ ወጪ የሚያድስ፣ የሚጠግን ወይም የሚያሻሽል ተከራይ ለዕድሳቱ፣ ለጥገናው ወይም ለማሻሻያ ያደረገው ወጪ ከንግድ ሥራ ገቢው ላይ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

**፴፫.ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረግ ስጦታ**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፬(፩) ለበጎ አድራጎት ዓላማ ለሚደረጉ ስጦታዎች የተፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ግብር ከፋዩ ራሱ ለሚያካሂደው የበጎ አድራጎት ተግባር ለሚያውለው ወጪ ጭምር ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪/ ለአዋጁ አንቀጽ ፳፬(፩)(ለ) አፈጻጸም በመንግስት የተደረገ ጥሪ ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት የሚደረግ ጥሪ ሲሆን በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚደረግ ጥሪን ይጨምራል፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም "በጎ አድራጎት ተግባር" ማለት ከታክስ ከፋይ ሠራተኞቹ ውጭ ለሌሎች ተረጂዎች የሚሰጥ የትምህርት፣ የጤና፣ የአካባቢ ጥበቃ ወይም ሌላ ሰብዓዊ እርዳታ ነው፡፡

**፴፬. በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል መሰረት ለተያዘ የንግድ ሥራ ሀብት የሚፈቀድ ተቀናሽ**

፩/ በካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል መሰረት ለተያዘ

2/ The limit to the deduction allowed pursuant to sub-article (1) of this Article shall be determined by a directive to be issued by the Minister.

**31. Business Promotion Expenditure**

The limit to the deduction of business promotion expenses incurred locally or abroad pursuant to Article 22(1)(a) of the Proclamation shall be determined by a directive to be issued by the Minister.

**32. A Lessee Maintaining or Repairing or Improving a Business Asset at his own Expense**

Expenditure incurred by a lessee of his own volition at variance with the terms of the contract concluded with the lessor in the maintenance or repair or improvement of the leased business asset shall be deducted from the business income of the lessee.

**33. Charitable Donation**

1/ A deduction allowed under Article 24(1) of the Proclamation for charitable donations shall apply to expenses incurred by the tax payer in the management of his own charitable activities.

2/ For the purpose of Article 24(1) (b) of the Proclamation, call by the government means call by the federal government or a regional state and includes a call by the Addis Ababa and Dire dawa city administrations.

3/ For the purpose of sub-article (1) of this Article "charitable donation" means a donation made in support of education, health, environmental protection or provided in the form of humanitarian aid other than for the tax payer's own employees.

**34. Deduction allowed for Business Asset held under Capital Goods Lease Agreement**

1/ Lease payment made for business asset held under

https://chilot.me



የንግድ ሥራ ሀብት የሚፈጸም የኪራይ ክፍያ ከጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀናሽ የተፈቀደለት ሰው በንብረቱ ላይ የእርጅና ቅናሽ አይታሰብለትም፡፡

**፴፭. <u>የዋና መሥሪያ ቤት ወጪ</u>**

በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ለሚሠራ ድርጅቱ ጥቅም ያደረገውን ትክክለኛ ወጪ ለመተካት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት የሚፈጽመው ክፍያ ተቀናሽ የሚደረገው፣ ወጪው የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት፣ ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠት ወይም የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል የተደረገ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የእርጅና ቅናሽ</u>**

**፴፮. <u>ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ግብር ከፋይ፤

ሀ) በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የሂሣብ ሪፖርት ሲያዘጋጅ አንድ ዓይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴ የተጠቀመ ከሆነ፣ እና

ለ) በባለቤትነት ለያዛቸው ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች ሁሉ አንድ ዓይነት የእርጅና ቅናሽ ዘዴ የተጠቀመ ከሆነ፣

በአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፩) መሠረት የሚፈቀድለትን የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፯ በተመለከተው ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፰ በተመለከተው ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት ሊወስን ይችላል፡፡

capital goods lease agreement is deductible business expenditure from gross business income.

2/ A person realizing deduction under sub-article (1) of this Article shall not be entitled to depreciation on the asset.

**35. <u>Head Office Expense</u>**

Payment made by a permanent establishment doing business in Ethiopia to its parent non-resident body in reimbursement of actual expenses incurred by the parent non-resident body for the benefit of the permanent establishment shall be deducted to the extent that such expense was incurred in deriving, securing or maintaining business income.

**<u>SUB-SECTION TWO</u>**

**<u>DEPRECIATION DEDUCTION</u>**

**36. <u>Depreciation Deduction of Depreciable Assets and Business Intangibles</u>**

1/ Subject to sub-article (2) of this Article, a taxpayer may determine the depreciation deduction allowed under Article 25(1) of the Proclamation according to the straight-line method under Article 37 of this Regulation or the diminishing value method under Article 38 of this Regulation provided:

a) the taxpayer has used the same method of depreciation in its financial accounts prepared in accordance with financial reporting standards; and

b) the same method of depreciation is used by the taxpayer for all depreciable assets owned by the taxpayer.

https://chilot.me



፪/ የሚከተሉት ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ መሰላት ያለበት በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ ብቻ ይሆናል:-

ሀ) ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች፤

ለ) በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ፡፡

፫/ በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ የእርጅና ቅናሽ ሲሰላ በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ ወጪ ማሻሻያው ያረፈበትን መሬት ወጪ መጨመር የለበትም፡፡

፬/ ማንኛውም ግብር ከፋይ "አስተላላፊ" ተብሎ ከሚጠራ ግንኙነት ያለው ሰው ላገኘው እና በአስተላላፊው ሙሉ የእርጅና ቅናሽ ላገኘበት ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የእርጅና ቅናሽ ማግኘት አይችልም፡፡

**፴፯.ቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ**

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፫) እና (፬) እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለአንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ህልዎት ለሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የተፈቀደው በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት የሚወሰን የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፱ የተመለከተውን መጣኔ በሀብቱ ወጪ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ይሰላል፡፡

፪/ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው የተያዘው የግብር ዓመት እና የቀደሙት የግብር ዓመታት ሁሉ ለአንድ ግብር ከፋይ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ወይም ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት የተፈቀደ ወይም የአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፬) ድንጋጌ ባይኖር ኖሮ ይፈቀድ የነበረ ጠቅላላ ተቀናሽ ወጪ ከሀብቱ ወጪ ሊበልጥ አይገባም፡፡

**፴፰. ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ**

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፫) እና (፬) እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለአንድ ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው

2/ The following assets shall be depreciated only under the straight-line method:

a) a business intangible;

b) a structural improvement of immovable property;

3/ For the purposes of calculating the depreciation deduction in relation to a structural improvement of immovable property, the cost of the structural improvement shall not include the cost of the land on which the improvement is situated.

4/ No depreciation deduction shall be allowed for the cost of a depreciable asset or business intangible acquired by a taxpayer from a related person ("transferor") when the cost of the asset or intangible had been fully depreciated by the transferor.

**37. Straight-line Depreciation**

1/ Subject to Article 25(3) and (4) of the Proclamation, the depreciation deduction allowed to a taxpayer for a tax year in respect of a depreciable asset or business intangible under the straight-line method shall be calculated by applying the rate specified in Article 39 of this Regulation against the cost of the asset.

2/ The total deductions allowed, or that would be allowed but for Article 25(4) of the Proclamation, to a taxpayer in respect of a depreciable asset or business intangible to which this Article applies for the current tax year and all previous tax years shall not exceed the cost of the asset.

**38. Diminishing Value Depreciation Deduction**

1/ Subject to Article 25(3) and (4) of the Proclamation,

https://chilot.me



ለሚቀንስ ሀብት የተፈቀደው ዋጋው እየቀነሰ በሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መሠረት የሚወሰን የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፱ የተመለከተውን መጣኔ በዓመቱ መጀመሪያ ባለው የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ተፈጻሚ በማድረግ ይሰላል፡፡

፪/ በአንድ የግብር ዓመት የአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፬) ድንጋጌ ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ ከሆነ፣ የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀብቱ በግብር ዓመቱ የንግድ ሥራ ገቢን ለማግኘት ብቻ ጥቅም ላይ እንደዋለ በመውሰድ ይሰላል፡፡

፫/ የግብር ከፋዩ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ቀሪ ዋጋ ከብር ሁለት ሺህ የማይበልጥ ከሆነ በአንድ ጊዜ በወጪነት ይያዛል፡፡

**፴፱.** **<u>የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች</u>**

፩/ ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ በሚከተሉት ምድቦች እና ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ተፈፃሚ ይደረጋል፤

the depreciation deduction allowed to a taxpayer for a tax year in respect of a depreciable asset under the diminishing value method shall be calculated by applying the rate specified in Article 39 of this Regulation against the net book value of the asset at the beginning of the year.

2/ If Article 25(4) of the Proclamation applies to a depreciable asset for a tax year, the net book value of the asset shall be calculated on the basis that the asset has been used in that year solely to derive business income.

3/ If the balance of a depreciable asset of the taxpayer is not more than two thousand Birr, the amount shall be fully deducted in the tax year to which the balance corresponds.

**39. <u>Rates of Depreciation Deduction</u>**

1/ The rates of depreciation applicable to a depreciable asset are specified in the following table based on the following categories:

https://chilot.me



| **ዋጋው የሚቀንስ ሀብት** | **የቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መጣኔ** |
|---|---|
| ኮምፒውተር፣ሶፍትዌር እና የመረጃ ማከማቻ መሣሪያ | 20 በመቶ |
| ግሪንሀውስ | 10 በመቶ |
| ግሪንሀ ውስን ሳይጨምር በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ | 5 በመቶ |
| ሌላ ማንኛውም ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | 15 በመቶ |
| ለማዕድን እና ነዳጅ የልማት ሥራዎች ጥቅም ላይ የሚውል ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | 25 በመቶ |

፪/ ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ:-

ሀ) የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ ሀያ አምስት በመቶ፣

ለ) በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ውጪ ለሆነ ከ አስር ዓመት በላይ ለሚያገለግል ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት አስር በመቶ፣ ወይም

ሐ) ለሌላ ማንኛውም ግዙፋዊ ሀልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት መቶ በመቶን ግዙፋዊ ሀልዎት ለሌለው ሀብት የአገልግሎት ዘመን በማካፈል የሚገኘው መጣኔ፣

ይሆናል።

፫/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም “የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ” ማለት ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚያወጣው በአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፯)(ሀ) ለ“ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች” በተሰጠው ትርጉም ተራ ቁጥር (፬) የተመለከተው ወጪ ነው።

| **Depreciable Asset** | **Straight -line Rate** |
|---|---|
| Computers, software, and data storage equipment | 20% |
| Greenhouses | 10% |
| Structural improvement on immovable property other than a greenhouse | 5% |
| Any other depreciable asset | 15% |
| Depreciable asset used in mining and petroleum development operations | 25% |

2/ The rate of depreciation applicable to a business intangible shall be:

a) for preliminary expenditure, 25%;

b) for a business intangible with a useful life of more than 10 years, other than a business intangible referred to in paragraph (a), 10%; or

c) for any other business intangible, 100% divided by the useful life of the intangible.

3/ In this Article, “preliminary expenditure” means expenditure referred to in paragraph (4) of the definition of “business intangible” in Article 25(7)(a) of the Proclamation incurred by a taxpayer before the commencement of a business.

https://chilot.me



**፵.በከፊል ለንግድ ስራ በዋለ ሕንጻ ላይ የሚታሰብ የእርጅና ቅናሽ**

አንድ ሕንጻ በንግድ ሥራ ሀብትነት በከፊል በሚያገለግልበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለንግድ ሥራ አገልግሎት በዋለው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

**፵፩.ጥገናዎችና ማሻሻያዎች**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማናቸውም ግብር ከፋይ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ላደረገው የጥገና ወይም ማሻሻያ ወጪ በግብር ዓመቱ የወጪ ተቀናሽ ይፈቀድለታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚፈቀደው የወጪ ተቀናሽ ሀብቱ በግብር ዓመቱ መጨረሻ ካለው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀያ በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

፫/ በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ የተደረገ የጥገና ወይም የማሻሻያ ወጪ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ሀያ በመቶ የሚበልጥ ከሆነ የጥገናው ወይም የማሻሻያው ሙሉ ወጪ በሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ ይጨመራል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሦስት**

**ኪሣራን ስለማሸጋገር**

**፵፪. ኪሣራን ስለማሸጋገር**

አንድ ግብር ከፋይ በአዋጁ አንቀጽ ፳፮፣ ፴፰፣ ወይም ፵፮ መሠረት የሚሸጋገር ኪሣራ፡-

፩/ ከአንድ የግብር ዓመት በላይ ያጋጠመው ከሆነ ግብር ከፋዩ መጀመሪያ የገጠመው ኪሣራ በቅድሚያ ይቀነስለታል፤

፪/ ኪሣራ ሊሸጋገር የሚችለው ኪሣራውን የሚያሳየው የግብር ከፋዩ የሂሣብ መዝገብ ኦዲት የተደረገ እና በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ብቻ ነው፤

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ግብር ከፋዩ፡-

**40. Depreciation allowed on a Building used Partially as a Business Asset**

Depreciation on a building used partially as a business asset shall be allowed only in proportion to the portion of the property used as a business asset.

**41. Repairs and Improvements**

1/ Subject to sub-article (2) of this Article, a taxpayer shall be allowed a deduction for a tax year for the cost of a repair or improvement made to a depreciable asset during the year.

2/ The amount of the deduction allowed under sub-article (1) of this Article shall not exceed twenty percent of the net book value of the asset at the end of the tax year.

3/ If the cost of a repair or improvement made to a depreciable asset during the year exceeds twenty percent of the net book value of the asset, the whole cost of the repair or improvement shall be added to the net book value of the asset.

**SUB-SECTION THREE**

**LOSS CARRY FORWARD**

**42. Loss Carry Forward**

1/ If a taxpayer has a loss carried forward under Articles 26,38 or 46 of the Proclamation for more than one tax year, the loss of the earliest year shall be deducted first.

2/ A loss may be carried forward only if the taxpayer's books of account showing the loss are audited and acceptable to the Authority.

3/ Despite sub-article (2) of this Article, a taxpayer may carry a loss forward if:

https://chilot.me



ሀ) ኪሣራ የሚያሳየውን በውጪ ኦዲተር ኦዲት የተደረገ የሒሣብ መዝገብ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ እንደሆነ፣ እና

ለ) የቀጣዩ የግብር ዓመት የታክስ ማስታወቂያ ማቅረቢያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት የታክስ ባለሥልጣኑ የግብር ከፋዩን የሂሣብ መዝገብ ኦዲት ማድረግ ያልቻለ እንደሆነ፣

ኪሣራውን ሊያሸጋግር ይችላል፤

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ የታክስ ባለሥልጣኑን በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፳፰ መሠረት ኪሣራውን በመመርመር የተሻሻለ የግብር ስሌት ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ የመስጠት መብቱን አያስቀርም፡፡

**፵፫. ኪሳራን ወደ ኃላ ሄዶ ስለማሸጋገር**

ለአዋጁ አንቀጽ ፴፪ አፈጻጸም ከረጅም ጊዜ ውል ጋር ተያይዞ የሚያጋጥም ኪሣራ ተካክሶ እስከሚያልቅ ድረስ ወደኃላ ሊሸጋገር ይችላል፡፡

**ንዑስ ክፍል አራት**
**የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም እና ኪሣራ**

**፵፬.የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም እና ኪሣራ**

፩/ ግብር ከፋይ ከውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ያገኘው ጥቅም በንግድ ሥራ ገቢው ውስጥ ይካተታል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እና የሚከተሉት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በአንድ የግብር ዓመት የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ የገጠመው ግብር ከፋይ ኪሣራውን በግብር ዓመቱ ከውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ካገኘው ጥቅም ጋር ማካካስ የሚችል ሲሆን፣

ሀ) ያላካካሰውን የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ መጠን በማንኛውም ጊዜ ካገኘው የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም ጋር በሙሉ እስኪካካስ ድረስ ኪሣራውን ላልተወሰነ ጊዜ ማሸጋገር ይችላል፤

a) the taxpayer has submitted books of account to the Authority showing that the loss has been audited by external auditors; and

b) the Authority has failed to audit the taxpayer's books of account before the due date for filing the taxpayer's tax declaration for the next following tax year.

4/ Nothing in sub-article (3) of this Article prevents the Authority from subsequently auditing the loss and serving the taxpayer with a notice of amended assessment in relation to the loss in accordance with Article 28 of the Federal Tax Administration Proclamation.

**43. Loss carry Backward**

For the purpose of Article 32 of the Proclamation, loss sustained in the performance of a long term contract may be carried backward until the loss is fully deducted.

**SUB-SECTION FOUR**
**FOREIGN CURRENCY EXCHANGE GAINS AND LOSSES**

**44. Foreign Currency Exchange Gains and Losses**

1/ A foreign currency exchange gain derived by a taxpayer shall be included in business income.

2/ Subject to sub-article (3) of this Article, if a taxpayer incurred a foreign currency exchange loss during a tax year, the loss shall be offset against a foreign currency exchange gain derived by the taxpayer during the year subject to the following:

a) the unused amount of a loss can be carried forward indefinitely for offset against foreign currency exchange gains until fully offset;

https://chilot.me



ለ)ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሣራ መጠን ባለሥልጣኑን በሚያሳምን አኳኋን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ የገጠመው የፋይናንስ ተቋም ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ተፈጻሚ የማይደረግ ሲሆን፣ የፋይናንስ ተቋሙ የደረሰበትን ኪሣራ መጠን ባለሥልጣኑን በሚያሳምን አኳኋን ማረጋገጥ ከቻለ የኪሣራው መጠን እንደተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡

፬/ ግብር ከፋይ የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሬ ጥቅም አገኘ ወይም ኪሣራ ገጠመው የሚባለው ጥቅሙ ወይም ኪሣራው እውን ሲሆን ነው፡፡

፭/ ግብር ከፋይ በውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም ማግኘቱን ወይም የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ ያጋጠመው መሆኑን ለመወሰን ከግብይቱ ጋር በተያያዘ ግብር ከፋዩ ራሱ ወይም ግንኙነት ያለው ሰው በገባው ከኪሣራ ሥጋት የመዳን ውል ያለው አቋም ከግምት መግባት ይኖርበታል፡፡

፮/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፣

ሀ) "የዕዳ ግዴታ" ማለት ገንዘብ ለሌላ ሰው ለመክፈል የተገባ ግዴታ ሲሆን ተከፋይ ሂሣብን እና ከቃልኪዳን ሰነዶች፣ ከሃዋላ ሰነዶች ወይም ከቦንዶች የሚመነጩ ግዴታዎችን ይጨምራል፤

ለ) "የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም" ማለት ከውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት ጋር በተገናኘ በውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዡቅ ምክንያት የተገኘ ጥቅም ነው፤

ሐ) "የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ" ማለት ከውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት ጋር በተገናኘ በውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዡቅ ምክንያት የደረሰ ኪሣራ ነው፤

መ) "የውጭ ሀገር ገንዘብ ግብይት" ማለት የንግድ

b) the taxpayer has substantiated the amount of the loss to the satisfaction of the Authority.

3/ Sub-article (2) of this Article shall not apply to a foreign currency exchange loss incurred by a financial institution and the amount of the loss shall be allowed as a deduction provided the financial institution has substantiated the amount of the loss to the satisfaction of the Authority.

4/ A taxpayer derives a foreign currency exchange gain or incurs a foreign currency exchange loss when the gain or loss is realised.

5/ In determining whether a taxpayer has derived a foreign currency exchange gain or incurred a foreign currency exchange loss in respect of a foreign currency transaction, account must be taken of the taxpayer's position under a hedging contract entered into by the taxpayer or by a related person in relation to the transaction.

6/ In this Article:

a) "debt obligation" means an obligation to make a payment of money to another person, including accounts payable and the obligations arising under promissory notes, bills of exchange, and bonds;

b) "foreign currency exchange gain" means a gain attributable to currency exchange rate fluctuations derived in respect of a foreign currency transaction;

c) "foreign currency exchange loss" means a loss attributable to currency exchange rate fluctuations incurred in respect of a foreign currency transaction;

d) "foreign currency transaction" means any of

https://chilot.me



ሥራ ገቢ ለማግኘት በሚከናወን የንግድ ሥራ ሂደት የተደረገ ከዚህ በታች የተመለከተ ማንኛውም ግብይት ነው፡-

(፩) በውጭ ሀገር ገንዘብ የሚደረግ ግብይት፤

(፪) በውጭ ሀገር ገንዘብ የተገለፀን የዕዳ ግዴታ መስጠት ወይም መቀበል፤ ወይም

(፫) በውጭ ሀገር ገንዘብ የተገለፀ ሌላ ማንኛውም ግብይት፤

ሠ) "ከኪሣራ ስጋት የመዳን ውል" ማለት አንድ ሰው በውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዠቅ ምክንያት ከሌላ ውል ጋር በተገናኘ በፋይናንስ ረገድ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልን ሥጋት ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የሚገባው ውል ነው፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል አምስት</u>**

**<u>ባንኮች እና የመድን ኩባንያዎች</u>**

**፵፭.<u>የባንኮች ኪሣራ መጠባበቂያ</u>**

ማንኛውም ባንክ በአንድ የግብር ዓመት ለኪሣራ የያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ሂሣብ በተቀመጠ የጥንቃቄ መሥፈርት መሠረት እስከተሰላ እና ከፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እስከሆነ ድረስ በግብር ዓመቱ የመጠባበቂያ ሂሣቡ መጠን ሰማንያ በመቶ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡

**፵፮. <u>የጠቅላላ መድን ኩባንያዎች ጊዜው ያላለፈ ሥጋት መጠባበቂያ</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ በአንድ የግብር ዓመት ጊዜው ላላለፈ ሥጋት የያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን በሂሣብ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተሰላ እስከሆነ ድረስ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚታየው ቀሪ የመጠባበቂያ ሂሣብ ለግብር ዓመቱ በተቀናሽ ወጪ ይያዝለታል፡፡

the following transactions entered into in the conduct of a business to derive business income:

(1) a dealing in a foreign currency;

(2) the issuing of, or obtaining a debt obligation, denominated in foreign currency; or

(3) any other dealing in which foreign currency is denominated;

e) "hedging contract" means a contract entered into by a person for the purpose of eliminating or reducing the risk of adverse financial consequences that might result for the person under another contract from currency exchange rate fluctuations.

**<u>SUB-SECTION FIVE</u>**

**<u>BANKS AND INSURANCE COMPANIES</u>**

**45. <u>Loss Reserve of Banks</u>**

A bank shall be allowed a deduction for a tax year for eighty percent of its loss reserve for the year, provided that the amount of the reserve has been calculated in accordance with the prudential requirements prescribed by the National Bank of Ethiopia and is consistent with financial reporting standards.

**46. <u>Reserve for Unexpired Risks of General Insurance Companies</u>**

1/ Subject to sub-article (2) of this Article, an insurance company carrying on the business of general insurance shall be allowed a deduction for a tax year of the balance of its reserve for unexpired risks as at the end of the year provided the amount of the reserve has been calculated in accordance with financial reporting standards.

፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ የመድን ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የመድን ሥራ የሚሠራ ከሆነ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተቀናሽ ወጪ የሚያዝለት መጠን ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ ጊዜው ላላለፈ ሥጋት በያዘው የመጠባበቂያ ሂሣብ የተወሰነ ይሆናል፡፡

፫/ ጠቅላላ መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ የአንድ ግብር ዓመት ንግድ ሥራ ገቢ እንደሁኔታው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት ባለፈው የግብር ዓመት በተቀናሽ ወጪ የተያዘለትን ጊዜያቸው ላላለፉ ሥጋቶች የያዘውን የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን ይጨምራል፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ጠቅላላ መድን" ማለት በንግድ ሕግ ከተገለፀው የህይወት መድን በስተቀር ማንኛውም መድን ነው፡፡

## ፵፯.የህይወት መድን ንግድ ሥራ ግብር የሚከፈልበት ገቢ

፩/ የህይወት መድን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ የመድን ኩባንያ የአንድ ግብር ዓመት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሰላል፡-

**(ሀ+ለ+ሐ+መ) -(ሠ+ረ+ሰ+ሸ)**

ለዚህም ቀመር አፈፃፀም፡-

"ሀ" የህይወት መድን ለገዙ ደንበኞች ኩባንያው የመለሰውን አረቦን ሳይጨምር በአንድ ዓመት ውስጥ ያገኘው የህይወት መድን አረቦን፤

"ለ" በዓመት ውስጥ ከህይወት መድን ሥራ ጋር በተያያዘ ኩባንያው ያገኘው የኢንቨስትመንት ገቢ፤

"ሐ" በዓመቱ ለተሰረዙ የህይወት መድን ፖሊሲዎች ኩባንያው ባለፉት ጊዜያት በተቀናሽ ወጪ የተያዘለት ማናቸውም የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን፤

2/ If an insurance company is a non- resident company carrying on business through a permanent establishment in Ethiopia, the deduction allowed under sub-article (1) of this Article shall be limited to the balance of the company's reserve for unexpired risks in Ethiopia.

3/ The business income of an insurance company carrying on the business of general insurance for a tax year shall include the amount of the company's reserve for unexpired risks deducted in the previous tax year under sub-article (1) or (2) of this Article, as the case may be.

4/ In this Article, "general insurance" means all insurance other than life insurance as defined in the Commercial Code.

## 47. Taxable Income from Life Insurance Business

1/ The taxable income of an insurance company from the conduct of the business of life insurance for a tax year shall be calculated according to the following formula:

$$(A + B + C + D) - (E + F + G + H)$$

where:

**"A"** is the life insurance premiums derived by the company during the year but not including premiums returned to policy holders during the year;

**"B"** is investment income derived by the company during the year relating to the business of life insurance;

**"C"** is the amount of any previously deducted reserves for life policies cancelled during the year;

"መ" ኩባንያው በዓመቱ ከህይወት መድን ሥራ ያገኘው ሌላ ማንኛውም ገቢ፤

"ሠ" ኩባንያው ከሚያካሂደው የህይወት መድን ሥራ ጋር በተያያዘ የኮሚሽን ክፍያዎችን፣ የጠለፋ ዋስትና አረቦንን፣ የሥጋት ትንተና ወጪዎችን፣ በፖሊሲው ላይ የሚጠየቁ የመንግሥት ክፍዎችን እና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን ጨምሮ በዓመቱ ከመድን ፖሊሲ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ያወጣው ወጪ፤

"ረ" በዓመቱ ላወጣቸው አዲስ የህይወት መድን ፖሊሲዎች የያዘውን መነሻ የመጠባበቂያ ሂሣብ ጨምሮ የያዘው ተጨማሪ የህይወት መድን ፖሊሲ መጠባበቂያ ሂሣብ፤

"ሰ" በዓመቱ ከተከፈሉ የህይወት መድን ፖሊሲዎች ጋር በተገናኘ ከያዘው ጠቅላላ የመጠባበቂያ ሂሣብ መጠን እና በዚሁ ሂሣብ ላይ ካገኘው ገቢ በላይ በህይወት መድን ፖሊሲዎች መሠረት ለቀረቡ የህይወት መድን ክፍያ ጥያቄዎች የፈፀመው ክፍያ፣ እና

"ሸ" ከህይወት መድን ሥራ ጋር በተገናኘ ኩባንያው በዓመቱ ውስጥ ያወጣው ሌላ ማንኛውም ተቀናሽ ወጪ ነው፡፡

፪/ አንድ ኩባንያ ከህይወት መድን ሥራ በተጨማሪ የጠቅላላ መድን ሥራን ጨምሮ በሌላ ማንኛውም የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ እንደሆነ ከህይወት መድን ሥራ የሚያገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከሌላው የንግድ ሥራ ገቢው ተለይቶ ለብቻው መሰላት አለበት፡፡

፫/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የህይወት መድን" በንግድ ሕግ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

**"D"** is any other income derived by the company during the year relating to the life insurance business;

**"E"** is underwriting expenses incurred by the company during the year in the conduct of life insurance business, including commissions paid, reinsurance premiums, risk analysis costs, Government charges on the policy, and operating expenses;

**"F"** is the additions to life policy reserves, including the initial reserve on new life policies issued during the year;

**"G"** is the amount of claim payments under life policies made in excess of the sum of reserved amounts and income earned on the reserved amounts in relation to life policies paid out during the year; and

**"H"** is any other deductible expenditure incurred by the company during the year in relation to the life insurance business.

2/ If a company conducts the business of life insurance and some other business including the business of general insurance, the taxable income of the company from the conduct of the life insurance business shall be calculated separately from the taxable income from other business of the taxpayer.

3/ In this Article, "life insurance" has the meaning given to the term in the Commercial Code.

https://chilot.me



## ንዑስ ክፍል ስድስት
## ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች

**፵፰.የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ**

ለአዋጁ አንቀጽ ፹፪ አፈጻጸም ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንደ ግለሰብ ተቆጥረው የዓመቱን የሽያጭ ገቢያቸውን መሠረት በማድረግ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

## SUB-SECTION SIX
## MICRO ENTERPRISES

**48. Obligation of Micro Enterprises to Maintain Books of Account**

For the purpose of Article 82 of the Proclamation, micro enterprises shall be treated as individual and the obligation to maintain books of account shall apply to such enterprises on the basis of their annual turnover.

## ንዑስ ክፍል ሰባት
## የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች

**፵፱. በግምት ላይ ተመስርቶ የሚከፈል የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የንግድ ሥራ ግብር**

፩/ በግምት ላይ ተመስርቶ የሚከፈል የደረጃ ‘ሐ’ ግብር ከፋዮች የንግድ ሥራ ግብር የሚሰላው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

፪/ የአንድ ግብር ከፋይ ዓመታዊ ግብር የሚሰላው የግብር ከፋዩ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ በሚወድቅበት የገቢ ማዕቀፍ ውስጥ ያለውን ዓመታዊ ከፍተኛ ጠቅላላ ገቢ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

፫/ ሚኒስትሩ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች የንግድ ሥራ ግብር የሚሰላበትን ሠንጠረዥ ቢያንስ በየሶስት ዓመቱ ማሻሻል አለበት፡፡

4/ የተሽከርካሪ ባለንብረት የሆነ ግብር ከፋይ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚጠቀምበትን ተሽከርካሪ ራሱ የሚያሽከረክር ከሆነ ሊከፍል የሚገባው ግብር ሲሰላ ሾፌር ቢቀጥር ኖሮ ሾፌሩ በቅጥር ገቢው ላይ ሊከፍል ይገባ የነበረው ግብር መታከል አለበት፡፡

## SUB-SECTION SEVEN
## CATEGORY ‘C’ TAX PAYERS

**49. Presumptive Business Tax of Category ‘C’ Taxpayers**

1/ The presumptive business tax to be paid by category “C” tax payers shall be calculated in accordance with the SCHEDULE attached to this Regulation.

2/ The annual taxable income of a tax payer shall be assessed in accordance with the maximum annual turnover in the income bracket within which the annual gross income of the tax payer falls.

3/ The Minister shall revise the schedule in accordance with which the tax to be paid by category “C” tax payers is assessed at least every three years.

4/ If a tax payer who is the owner of a vehicle, drives the vehicle he uses in the business of rendering transport service, the employment income tax that the driver would have paid had the owner employed such driver, shall be included in calculating the tax payable by the owner of the vehicle.

https://chilot.me



## ክፍል ስድስት

## የሠንጠረዥ “መ” ገቢ

**፶. አልፎ አልፎ ሀብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ**

ለአዋጁ አንቀጽ ፶፰ አፈጻጸም “አልፎ አልፎ ሀብትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ” ማለት በንግድ ሥራ ላይ በመደበኛነት ያልተሰማራ ሰው የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን አልፎ አልፎ በማከራየት የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ነው፡፡

**፶፩.በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወደ ውጭ የሚልከው ትርፍ**

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት ወደ ውጭ በሚልከው ትርፍ ላይ በአዋጁ አንቀጽ ፷፪ መሠረት ግብር የሚጣለው የድርጅቱን የግብር ዓመት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

፪/ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወደ ውጭ የሚልከው ትርፍ በሚከተለው ቀመር መሠረት ይሠላል፡-

**ሀ+(ለ-ሐ)-መ**

ለዚህም ቀመር አፈፃፀም፡-

“ሀ” በግብር ዓመቱ መጀመሪያ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ያለው ጠቅላላ የተጣራ ዋጋ፤

“ለ” በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት የተሰላ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት የግብር ዓመቱ የተጣራ ትርፍ፤

“ሐ” በግብር ዓመቱ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ባገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ የሚከፈለው የንግድ ሥራ ገቢ ግብር፤ እና

“መ” በግብር ዓመቱ መጨረሻ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ያለው ጠቅላላ የተጣራ ዋጋ፤

ነው፡፡

## SECTION SIX

## SCHEDULE ‘D’ INCOME

**50. Income from Casual Rental of Asset**

For the purpose of Article 58 of the Proclamation “income derived from casual rental of asset” means gross income derived by a person who is not engaged in the regular business of rental of movable or immovable asset.

**51. Repatriated Profit of a Permanent Establishment**

1/ The tax under Article 62 of the Proclamation on the repatriated profit of a non-resident body conducting business through a permanent establishment in Ethiopia shall be imposed by reference to the body’s tax year.

2/ The repatriated profit of a body for a tax year shall be calculated in accordance with the following formula:

**A + (B - C) – D**

where:

**“A”** is the total cost of assets, net of liabilities, of the permanent establishment at the commencement of the tax year;

**“B”** is the net profit of the permanent establishment for the tax year calculated in accordance with the financial reporting standards;

**“C”** is the business income tax payable on the taxable income of the permanent establishment for the tax year; and

**“D”** is the total cost of assets, net of liabilities, of the permanent establishment at the end of the tax year.

https://chilot.me



፫/ በአንድ የግብር ዓመት በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት ወደ ውጭ ለሚልከው ትርፍ ስሌት በግብር ዓመቱ መጨረሻ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ጠቅላላ ዋጋ በቀጣዩ የግብር ዓመት መጀመሪያ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት ሀብት ያለው ጠቅላላ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

**፶፪. የንግድ ትርፍ መጠን መስተካከሉ በተከፋፋለ ትርፍ ድርሻ ላይ የሚኖረው ውጤት**

አንድ ድርጅት ለባለስልጣኑ ያሳወቀው የንግድ ሥራ ትርፍ መጠን ባለስልጣኑ ባደረገው ኦዲት ከደረሰበት ግኝት ያነሰ መሆኑ ድርጅቱ ባሳወቀው ትርፍ ላይ ተመስርቶ ለባለአክስዮኖች ባከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ላይ በተከፈለው ግብር ላይ ውጤት አይኖረውም፡፡

**፶፫. የካፒታል ሀብቶችን በስጦታ በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚከፈል ግብር**

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፶፱ አፈጻጸም የካፒታል ሀብትን በስጦታ በማስተላለፍ የሚከፈለው ታክስ የሚታሰበው በስጦታ በተላለፈው ንብረት የመጀመሪያ ዋጋ እና ንብረቱ በስጦታ በተላለፈበት ጊዜ ባለው ዋጋ መካከል በሚታየው ልዩነት ላይ ነው፡፡

፪/ የካፒታል ሀብቶችን በስጦታ በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ የተቀባዩ ነው፡፡

**ክፍል ሰባት**

**ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ**

**፶፬. ከገቢ ግብር ነጻ የሆነ ገቢ**

፩/ የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው:-

ሀ) በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች ለእውቀት ሽግግር ከውጭ ሀገር ለሚያስመጧቸው ባለሙያዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚከፈላቸው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤

3/ In calculating the repatriated profit of a permanent establishment for a tax year, the total cost of assets of the permanent establishment at the end of a tax year shall be the total cost of assets at the commencement of the next following tax year.

**52. The Effect of Adjustment of Business Profit on Paid out Dividends**

The fact of a business profit declared by a body being less than the adjusted business profit of the body by the authority in accordance with the finding of a tax audit, shall not affect the tax on dividend distributed to shareholders on the basis of the profit declared by that body.

**53. Capital Gains Tax Payable on the Disposal of Certain Investment Assets by Donation**

1/ For the purpose of Article 59 of the Proclamation, tax payable on a capital asset disposed by donation shall be calculated on the difference between the original cost of the asset and the cost of the asset at the time of disposal by donation.

2/ The receiver of donation shall be liable to pay tax on a capital asset disposed by donation.

**SECTION SEVEN**

**EXEMPT INCOME**

**54. Exempt Income**

1/ The following items of income are exempt from income tax:

a) employment income of not exceeding five years paid to expatriate professionals recruited for transfer of knowledge by investors engaged in export business in accordance with a directive to be issued by the Minister;

https://chilot.me



ለ) በአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ አንድ ሰው በተደጋጋሚ ለአንድ ቀጣሪ የሰጠው አገልግሎት ሲደመር ከአንድ ወር የሚበልጥ ከሆነ ተቀጣሪው የሚከፍለው ግብር የሚታሰበው በመጨረሻው ቅጥር ባገኘው ገቢ ላይ ብቻ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማንኛውም የአስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ቀጣሪ ሳያቋርጥም ሆነ በተደጋጋሚ ከሠላሳ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ያገለገለ ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ የሚያገኘው ገቢ፤

ሐ) ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ለ) አፈጻጸም "ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ" ማለት መደበኛ የሙያ ሥልጠና ያልወሰደ ልዩ ሙያ በሚጠይቁ ማሽኖችና መሣሪያዎች የማይጠቀም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ከ30 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የተቀጠረ ግለሰብ ነው፡፡

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፷፭(፩) ሀ(፩) መሠረት ከግብር ነጻ የተደረገው አሠሪው ሠራተኛው ሲታመም ለሠራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ በሠራተኞች የጤና መድን አቅድ መሠረት አሠሪው ለሠራተኞች ጥቅም የሚከፍለውን አረቦን ይጨምራል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ሀብቶች

**፶፭. ሀብትን ማስተላለፍ እና በባለቤትነት መያዝ**

ለእርጅና ቅናሽ እና የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ለሚከፈል ግብር ዓላማ ምዝገባ የሚፈጸምበት ሀብት በሽያጭ፣ በልውውጥ ወይም በስጦታ ሲተላለፍ አስተላላፊው ሀብቱን እንዳስተላላፈ የሚቆጠረው እና የተላለፈለት ሰው ሀብቱን በባለቤትነት እንደያዘ የሚቆጠረው የሽያጭ፣ የልውውጥ ወይም የስጦታ ውሉ ውል ለመዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

b) income from employment received by unskilled employee working for the same employer whether continuously or intermittently for not more than thirty (30) days within any twelve month period; provided, however, that the tax payable on income from employment received by a casual employee working intermittently for the same employer for more than thirty (30) days within twelve months period shall be calculated only on the income received by that employee from the last employment;

c) for the purpose of the exemption under paragraph (b) of this sub-article "unskilled employee" means an employee who has not received vocational training, does not use machinery or equipment requiring special skill, and who is engaged by an employer for a period aggregating not more than thirty(30) days during a calendar year.

2/ The exemption accorded under Article 65(1)( a) (1) of the Proclamation to an amount paid by an employer to cover the cost of medical treatment of an employee shall include premium payments made by an employer on behalf of an employee under employees' medical insurance scheme.

## SECTION EIGHT
## ASSETS

**55. Disposal and Acquisition of Asset**

For the purpose of depreciation and capital gain tax, when a registerable asset is transferred by sale, exchange or gift, the transferor is treated as having disposed of the asset and the transferee is treated as having acquired the asset at the time the contract of sale, exchange or gift is registered by an entity empowered to exercise the function of the notary.

**፶፮.<u>ዋጋ</u>**

፩/ በአዋጁ የተመለከተው የምድብ "ሀ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት ዋጋ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ይደረግበታል፡፡

፪/ አንድ ግብር ከፋይ በባለቤትነት የሚይዘው ሀብት:-

ሀ) በአዋጁ መሠረት ግብር በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለል የገንዘብ መጠን ከሆነ፣ የሀብቱ ዋጋ ሀብቱን በባለቤትነት ለመያዝ በግብር ከፋዩ የተከፈለን ማንኛውንም የገንዘብ መጠን እና ግብር በሚከፈልበት ገቢ ውስጥ የሚጠቃለለውን የገንዘብ መጠን ይጨምራል፤ ወይም

ለ) ከግብር ነጻ የሆነ ገቢ ከሆነ፣ የሀብቱ ዋጋ ሀብቱን በባለቤትነት ለመያዝ በግብር ከፋዩ የተከፈለን ማንኛውንም የገንዘብ መጠን እና ከግብር ነጻ የሆነውን የገንዘብ መጠን ይጨምራል፡፡

**፶፯.<u>የአክስዮን መተላለፍ</u>**

በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የሚያስተላልፈው አክስዮን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተገናኘ ከሆነ አክስዮኑ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደተላላፈ ይቆጠራል፡፡

**<u>ክፍል ዘጠኝ</u>**

**<u>አስተዳደራዊ እና የሥነ-ሥርዓት ደንቦች</u>**

**፶፰. <u>በደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የሚያዝ የሂሳብ ሰነድ</u>**

፩/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በቀላል የሂሳብ አያያዝ ዘዴ ከሚይዙት የሂሳብ መዝገብ ጋር አያይዘው የሚያቀርቡትን ሰነድ ባለስልጣኑ በመመሪያ ይወስናል፡፡

፪/ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች የተመለከተውን መስፈርት አሟልተው የተገኙ እንደሆነ በፈቃደኝነት በአክሩዋል የሂሣብ አያያዝ ዘዴ ሂሣባቸውን መያዝ ይችላሉ፡፡

**56. <u>Cost</u>**

1/ The cost of a class 'A' taxable asset provided in the Proclamation shall be adjusted for inflation as determined under a directive issued by the Minister.

2/ If the acquisition of an asset by a taxpayer is the derivation of an amount that is:

a) included in the income of the taxpayer subject to tax under the Proclamation, the cost of the asset is the amount so included plus any amount paid by the taxpayer for the asset; or

b) exempt income, the cost of the asset is the exempt amount plus any amount paid by the taxpayer for the asset.

**57. <u>Transfer of share</u>**

If a share that a non-resident person transfers is related directly or indirectly with an asset in Ethiopia, such share shall be treated as having been transferred in Ethiopia.

**<u>SECTION NINE</u>**

**<u>ADMINISTRATIVE AND PROCEDURAL RULES</u>**

**58. <u>Books of Account to be kept by Category 'B' Tax Payers</u>**

1/ The Authority shall determine by directive the documents that category "B" tax payers shall be required to submit together with their simplified books of account.

2/ Category "B" taxpayers may voluntarily account on accrual basis provided that they comply with the requirements set under financial reporting standards.

https://chilot.me



**፶፱. <u>በደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የሚያዝ የሂሳብ መዝገብና ሰነድ</u>**

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፹፪(፫) አፈጻጸም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ሊይዙ የሚገባውን የሂሳብ መዝገብ ሊይዙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዓይነት መዝገብ የያዙ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ግብር የሚወሰነው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ መዝገባቸው መሠረት ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ ሠራተኛ የሚቀጥር ከሆነ ለሠራተኛው የሚከፍለውን ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እና ከዚሁ ገቢ ላይ ቀንሶ የሚያስቀረውን ማንኛውንም ግብር የሚያሳይ ሰነድ መያዝ አለበት፡፡

**፷. <u>በደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የሚከፈል ግብር</u>**

፩/ ለአዋጁ አንቀጽ ፵፱ አፈጻጸም የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በዓመታዊ የሽያጭ መጠን ላይ የተመሰረተ የግምት መደበኛ የቁርጥ ግብር ወይም አመላካች ባላቸው የንግድ ሥራ ዘርፎች የቁርጥ ግብር ዘዴዎች መሰረት ግብር ይከፍላሉ፡፡

፪/ በትራንስፖርት የንግድ ሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ ቀንሰው የሚያስቀሩትን ግብር የሚከፍሉት ከንግድ ሥራ ትርፍ ግብር ጋር በአንድነት ይሆናል፡፡

**፷፩.<u>ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ግብርን ተቀናሽ ስላለማድረግ</u>**

ለአዋጁ አንቀጽ ፺፪ አፈጻጸም ሚኒስትሩ፡-

፩/ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ የመያዝ ሥርዓት ተፈጻሚ የማይደረግባቸውን የአገልግሎት ዓይነቶች፣

፪/ ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ የማይመለከታቸውን ሰዎች

በመመሪያ ይወስናል፡፡

**59. <u>Books of Account and Documents to be Kept by Category 'C' Taxpayers</u>**

1/ For the purpose of Article 82(3) of the Proclamation, Category "C" tax payers may keep book of accounts that Category "B" tax payers are required to maintain. The tax of Category "C" tax payers maintaining books of account shall be assessed in accordance with such books of account as are acceptable to the Authority.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, a Category "C" tax payer employing a worker shall keep documents showing any amount of employment income paid to the employee and any amount withheld in tax from such income.

**60. <u>Payment of Tax by Category 'C' Tax payers</u>**

1/ For the purposes of Article 49 of the Proclamation, Category "C" tax payers shall pay tax in accordance with turn over based standard presumptive business tax or indicator based presumptive business tax methods.

2/ Category "C" taxpayers engaged in the business of transport service shall pay the withholding tax from employment income together with their business income tax.

**61. <u>Non- Applicability of Withholding Tax</u>**

For the purpose of Article 92 of the Proclamation, the Minister shall specify by a directive:

1/ the type of services to which withholding tax shall not apply;

2/ persons to whom the obligation to withhold tax shall not apply.

https://chilot.me



**፷፪.በሀገር ውስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፺፪ መሠረት ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው በዚሁ አንቀጽ መሠረት ግብር ተቀንሶ ክፍያ ለሚፈጸምለት ሰው ተከታታይ ቁጥር ያለው ሕጋዊ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡

፪/ ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው የመንግሥት ተቋም ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ደረሰኝ በሚኒስቴሩ የተፈቀደ መሆን አለበት፡፡

፫/ ከመንግሥት ተቋም በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ላለበት ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፷፫.ግብርን ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ላለበት ሰው የንግድ ፍቃድ የማቅረብ ግዴታ**

በአዋጁ አንቀጽ ፺፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ከሚቀርበው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በተጨማሪ ማንኛውም ግብር ከፋዩ የንግድ ፈቃድ የማቅረብ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

**፷፬. ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ መያዝ ስላለበት ሰው ኃላፊነት**

፩/ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ለባለስልጣኑ የማስተላለፍ ግዴታ የተጣለበት ሰው ግዴታውን ያልተወጣ ቢሆንም ግብር ከፋዩ ግብሩን የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ የአዋጁ አንቀጽ ፺፯(፫) ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፩፻፮(፩) የተጣለውን ቅጣት አያስቀርም፡፡

**62. Withholding of Tax from Domestic Payments**

1/ A withholding agent required to withhold tax under Article 92 of the Proclamation shall issue a serially numbered official receipt to the recipient of the payment from which tax is to be withheld under that Article.

2/ If the withholding agent is a Government agency, the receipts referred to in sub-article (1) of this Article shall be authenticated by the Ministry.

3/ Article 19 of the Federal Tax Administration Proclamation shall apply to receipts referred to in sub-article (1) of this Article issued by a withholding agent other than a Government agency.

**63.Requirement to provide Trade License to a Withholding Agent**

Apart from the requirement of Tax Identification Number (TIN) laid down in Article 92 sub-article (4) of the Proclamation, a tax payer shall also be required to submit his trade license.

**64. The Liability of a Withholding Agent**

1/ Article 97(3) of the Proclamation shall not apply where a withholding agent required to withhold and transfer tax to the Authority under the Proclamation presents evidence to the tax authority that the principal tax payer has paid the tax, notwithstanding that the withholding agent has failed to withhold and transfer the tax.

2/ The provision of sub-article (1) of this Article does not preclude the penalty imposed under Article of 106(1) of the Tax Administration Proclamation.

https://chilot.me



**፷፭.** **<u>ዘግይቶ ስለሚቀርብ የሂሳብ መዝገብ</u>**

፩/ የሂሳብ መዝገብ ዘግይቶ በመቅረቡ ምክንያት ተቀባይነት አያጣም፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ፡-

ሀ) የሂሳብ መዝገብ ባለመቅረቡ ምክንያት በግምት በተወሰነ ግብር ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

ለ) በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፩፻፪ የተጣለውን ቅጣት አያስቀርም፡፡

**፷፮.** **<u>የንግድ ሥራ ከተቋረጠ በኋላ የሚገኝ ገቢ</u>**

ለአዋጁ አንቀጽ ፸፬ አፈጻጸም ገቢን የሚያስገኝ የንግድ ሥራ ያቆመ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፍልበት አሠራር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል አስር</u>

## <u>ልዩ ልዩ</u>

**<u>፷፯</u>.** **<u>በቡድን የተያዙ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች</u>**

፩/ አዋጁ ተፈጻሚ መሆን በጀመረበት ጊዜ በቡድን የተያዘ ቀሪ የእርጅና ቅናሽ ያለው ግብር ከፋይ ቀሪውን የእርጅና ቅናሽ በተሻረው አዋጅ መሠረት ያገኛል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተፈጻሚ የሚሆንበት ግብር ከፋይ በቡድን የተያዙ ቀሪ የእርጅና ቅናሽ ውስጥ ያለን ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ያስተላለፈ እንደሆነ፣ የእርጅና ቅናሽ ስሌት መሠረቱ ሀብቱን በማስተላለፍ ባገኘው ጥቅም መጠን ይቀንሳል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ዋጋው የሚቀንስ ሀብት በመተላለፉ ምክንያት የቡድኑ የእርጅና ቅናሽ የስሌት መሠረት ከዜሮ በታች የገንዘብ መጠን የሚኖረው ከሆነ፡-

ሀ) ከዜሮ በታች የሚታየው የገንዘብ መጠን በግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ይጨመራል፤ እንዲሁም

**65.** **<u>Delayed Submission of Books of Account</u>**

1/ Books of account shall not be rejected by more reason of late submission.

2/ The provision of sub-article (1) of this Article shall:

a) not apply where the tax has been assessed by estimation because of non-filing of tax return;

b) not preclude the penalty imposed under article 102 of the Tax Administration Proclamation.

**66.** **<u>Income Derived after Ceasing of Business</u>**

For the Purpose of Article 74 of the Proclamation, the Tax Authority shall issue a directive on the procedure of payment of tax by a tax payer deriving income after ceasing business.

## <u>SECTION TEN</u>

## <u>MISCELLANEOUS</u>

**67.** **<u>Pooled Depreciable Assets</u>**

1/ A taxpayer who has a positive balance in a depreciation pool at the commencement of the Proclamation shall continue to depreciate the balance of the pool in accordance with repealed Proclamation.

2/ If a taxpayer to whom sub-article (1) of this Article applies disposes of a depreciable asset in a depreciation pool, the consideration for the disposal shall reduce the depreciation base of the pool.

3/ If, as a result of a disposal a depreciable asset referred to in sub-article (1)of this Article, the depreciation base of a depreciation pool is a negative amount:

a) the negative amount is included in business income; and

https://chilot.me



ለ) የቡድኑ የእርጅና ቅናሽ ሂሣቡ ተዘግቶ በቡድኑ ውስጥ የቀረ ማንኛውም ሀብት የእርጅና ቅናሹን እንደጨረሰ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

፬/ አዋጁ ተፈጻሚ መሆን በጀመረበት ቀን ወይም ከዚያ በኋላ ዋጋው የሚቀንስ ሀብት ባለቤት የሆነ ግብር ከፋይ የእርጅና ቅናሽ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፰ መሠረት የሚሰላለት ሲሆን፣ የሀብቱ ወጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው በቡድኑ የተያዘ ቀሪ የእርጅና ቅናሽ ውስጥ አይካተትም፡፡

**፷፰. <u>የንግድ ሥራ ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>**

፩/ በተሻረው አዋጅ መሠረት ተቀናንሶ ያላለቀ የንግድ ሥራ ኪሣራ ያለው ግብር ከፋይ የእርጅና ቅናሹ በተሻረው አዋጅ መሠረት ሙሉ በሙሉ ያልተቀናነሰ ከሆነ ቀሪው ኪሣራ በተሻረው አዋጅ መሠረት ይቀነስለታል፡፡

፪/ ለአዋጁ አንቀጽ ፳፮(፬) አፈጻጸም በተሻረው ሕግ ያጋጠመ ማንኛውም ኪሣራ ከግምት ውስጥ አይገባም፡፡

**፷፱. <u>በመመሪያዎች የተፈቀዱ የግብር ነጻ መብቶች</u>**

አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በሚኒስትሩ በወጣ መመሪያ የተፈቀደ ከግብር ነጻ የመሆን መብት:-

፩/ በመመሪያው መሠረት መብቱ ተፈጻሚ መሆን እስከሚያበቃበት ቀን፣ ወይም

፪/ መመሪያው በሚኒስትሩ እስከሚሻርበት ቀን፣

ከሁለቱ እስከቀደመው ጊዜ ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

**፸. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር ፸፰/፲፱፻፺፬(እንደተሻሻለው) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ የተሻረው ደንብ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ለነበረው የግብር ዓመት ተፈጻሚ መሆኑ ይቀጥላል፡፡

b) the pool is treated as closed and any assets remaining in the pool are treated as fully depreciated.

4/ A taxpayer who has acquired a depreciable asset on or after the commencement of the Proclamation shall depreciate the asset in accordance with Article 38 of this Regulation and the cost of the asset shall not be added to a depreciation pool referred to in sub-article (1) of this Article.

**68. <u>Business Loss Carried Forward</u>**

1/ A taxpayer who has a business loss under the repealed Proclamation that has not been fully deducted under the repealed Proclamation shall continue to be deducted in accordance with the repealed Proclamation.

2/ Any loss incurred under the repealed Proclamation shall not be taken into account for the purposes of Article 26(4) of the Proclamation.

**69. <u>Exemptions under Directives</u>**

An exemption provided for in a Directive issued by the Minister prior to the commencement of the Proclamation shall remain in force until the earlier of:

1/ the date that the Directive lapses according to its terms; or

2/ the date that the Minister repeal the Directive.

**70. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ The Income Tax Regulation No. 78/2002 (as amended) are repealed by this Regulation.

2/ The repealed Regulation shall continue to apply for tax years preceding the effective date of this Regulation.

https://chilot.me



፸፩. **ደንቡ የሚፀናበት ቀን**

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**71. Effective Date**

This Regulation shall apply on income derived as of 8th day of July, 2016.

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, this 24th day of August 2017.**

**ኃይለማሪያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me

https://chilot.me